ለኪዳናዊ ወንድሜና የአገልግሎት ባልደረባዬ አክሊለ ጊዮርጊስ!

ሙሉ ደኅንነትህን፡ ከጦማርህ በማወቄ፡ ደስ ብሎኝ፤ እኔም፡ በኹለንተናዊ ጤንነት ላይ ስለምገኝ፡ ለፈጣሪዬ፥ ለቅድስት እናቱም፡ የምስጋና ቍርባንን እያቀረብሁ አለሁ።

ወደዋናው የመልስ ጽሑፌ ከመግባቴ በፊት፡ በጦማርህ ውስጥ ስላገኘሁት፡ አንዲት ነገር፡ የምልህ አለኝ፤ እርሱም፡ "ኪዳናዊ ወንድምህ መኾኔን፡ በሃይማኖት ተቀብለህ፡ "ጋሽዬ!" ብለህ፡ በእግዚአብሔር እውነት ካቀረብኸኝ በኋላ፡ ምነው ታዲያ፡ "እባክዎ!" በሚለው፡ በተቃራኒው የአንቱታ ግብዝነት አራቅኸኝ!?" በሚል ቃል ልገልጽልህ የፈለግሁት ትችቴ ነው።

ይኼ ዓይነቱ <u>*የለብታ*</u> አቋምና አካኼድማ፡ በእኛ በእውነተኞች ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ ፈጽሞ ቦታ ሊኖረው አይገባም፤ ስለዚህ፡ ይኸው ተፃራሪ ድርጊት፡ ለወደፊቱ፡ በማንኛችንም በኩል እንደማይደገም አምናለሁ። (ራእ. ፫፥ ፲፰-፳፱።)

"ኤር<u>ሚ</u>ያስ" የሚለውም፡ የአጻጻፍ ስሕተት፡ "ኤር<u>ም</u>ያስ" በሚለው ሆሄ ይስተካከል ዘንድ፡ እርማቱን፡ በትሕትና አቅርቤአለሁ።

ይህን ካልሁ በኋላ፡ ዓቢይ ስለኾነው፡ ስለጥያቄዎችህ ቍም ነገር፡ ያለኝን መልስ ወደመስጠቱና ከዚህ የተነሣ የተላለፈውን ልዩ መልእክት ወደማቅረቡ እኼዳለሁ።

## መግቢያ

አንተን ለመሰሉት እውነተኞች ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች፡ እጅጉን ፈታኝና የመልካሙ እግዚአብሔራዊ ሕይወት፡ ተፃራሪ የኾኑትን፤ በጊዜውም መፍትሔ ተገኝቶላቸው ሊወገዱ የሚገባቸውን፡ እንዲህ ዓይነቶቹን የህልውና ጠንቆችን የያዙ ጥያቄዎችን፡ በግልጽ በማቅረብህ፡ "እግዜር ይስጥህ!" እያልሁ፡ አድናቆቴንና ምርቃቴን፡ በቅድሚያ አበረክትሃለሁ።

ቀጥዬም፡ የ፯ሺ፭፻፲፯ ዓመታት ዕድሜ ባለው፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን መሠረት፡ አንተም፥ እኔም የምናገለግላት፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ለኹለቱ ጥያቄዎችህ፡ ያሏትን መልሶች፡ አንባቢዎቻችን ጭምር፡ ይጠቀሙበት ዘንድ፡ በተመጠነ ሓተታ፡ እንደሚከተለው አቀርብልሃለሁ፡-

# ቅዱሱ ኪዳን፡
## ስለአንዲቷ ዘላለማዊት ሰንበት የሚለው።

፩ኛ. በኦሪታውያንና በወንጌላውያን ዘንድ፡ "ቅዳሜ" በምትባለው፥ በኪዳናውያንና በኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ ግን፡ በተከታይዋ ዕለተ እሑድ፡ በዘለዓለማዊትነቷ በቀጠለችው፥ አንዲት በኾነችው፡ በሰባተኛዪቱ የሰንበት ቀን፡ እውነተኛውን፡ የመንፈስ ቅዱስ አምልኳችንን ተከትለን፡ በግላችን እና/ወይም፡ በኅብረት፡ "መልካም ነው!" የምንለውን፡ ማናቸውንም ዓይነት አገልግሎት (ተግባር/ሥራ) መፈጸም እንችላለን።

ይህንኑም፡ መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠን፡ እንዲህ የሚለው መለኮታዊ መመሪያው፡ ያረጋግጥልናል፤ "ሰንበትሰ፡ በእንተ ሰብእ ተፈጥረት፤ ወአኮ ሰብእ፡ በእንተ ሰንበት። ወወልደ እጓለ እመሕያው ውእቱ፡ እግዚአ ለሰንበት።" ማለትም፡ "ሰንበት፡ ስለሰው ተፈጥሮአል እንጂ፡ ሰው፡ ስለሰንበት አልተፈጠረም። የማርያም ልጅም፡ የሰንበት ጌታዋ ነው!" ደግሞም፡ "ይከውንኬ በሰንበት፡ ገቢረ ሠናይ።" ማለትም፡ "ስለዚህ፡ በሰንበት፡ መልካም መሥራት ይገባል!" ባለበት፡ በዚሁ፡ መመሪያው ውስጥ፡ "ምጽዋተ አበድር፡ እመሥዋዕት!" ማለትም፡ "ለእኔ፡ መሥዋዕትን ከምታቀርቡልኝ ይልቅ፡ ለተቸገረው፡ ምጽዋትን ብትሰጡልኝ [ማለትም፡ ምሕረትን ብታደርጉለት] እወድዳለሁ!" ብሎ የጠቀሰው የነቢያት ቃሉ፡ የ"ምጽዋት" ሥርዓት፡ በትክክለኛው መልኩ፡ የሚፈጸምበት ምግባር፡ እንዲህ መኾኑን ያመለክተናል። (ማቴ. ፲፪፥ ፩-፲፪። ማር. ፪፥ ፳፯-፳፰።)

እዚህ ላይ፡ *"አኹንም እንደኦሪቱ፡ ሸክም ኾነው፡ ሲደረጉ የሚታዩ"* ካልኻቸው፡ ከብዙዎቹ ግዳጆች መካከል፡ በምሳሌነት በማውሳት፡ *"እንደጾም እና እንደበዓል ቀን ኹሉ፡ የባለቃል ኪዳን ባለትዳሮች ምንጣፍ፡ በሰንበትም ይከለከላልን?"* በሚል አገላለጽ ላቀረብኸው ጥያቄ፡ መልሱ፡ በዚሁ መልክ፥ ከዚሁ፡ ከሰንበቱ ርእስ ጋር፡ እንዲህ በሚል ቃል፡ የተጠቃለለ ኾኖ ይሰሰጣል።

በኪዳናውያንና በኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ ጋብቻም ኾነ፥ ሩካቤ ሥጋውን ጨምሮ፡ የባልና ሚስቱ መኻታ፥ ፍጹም የተቀደሰ ስለኾነ፡ በመካከላቸው ካለው፡ እግዚአብሔራዊ አንድነት የተነሣ፡ ጾምን ኾነ፥ በዓልን፥ ወይም፡ ሰንበትን፥ ወይም፡ ሌላውን፡ የግልና የጋራ ጉዳያቸውን በሚመለከት፡ ሌላ ሦስተኛ ሰው ሳይገባባቸው፡ ኹለቱ ባለትዳሮች፡ መንፈስ ቅዱስን ብቻ ይዘውና ተስማምተው፡ በፈቃዳቸው ከሚወስኑት በቀር፡ በአንዳቸው፥ ወይም፡ በኹለቱም በኩል፡ ቅዱሱ የፈቃደ ሥጋ ፍላጎታቸው በሚነሣሣባቸው ጊዜ፡ ንጹሑንና ቅዱሱን የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት፡ በማናቸውም ጊዜ፡ በፍጹም ፍቅርና ነጻነት፥ ደስታና እርካታ፡ ከመፈጸም የሚከለክላቸው፡ አንዳችም ምክንያት፡ ከቶ የለም።

# ቅዱሱ ኪዳን፡
# "የወሊድ መቆጣጠር"ን ሲገመግም።

፪ኛ. "‹‹የወሊድ መቆጣጠሪያ›› ተብሎ፡ ከአሕዛቡ ዓለም መንጭቶ፡ ‹ሕዝብ› የተባሉት *የፈጣሪ ወገኖች፤ ‹ክርስቲያን ነን›፤ ‹ቤተ ክርስቲያን ነን› የሚሉት ሳይቀሩ፤ በተለይ፡ ‹ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ነን› በምንለው ዘንድ ሳይቀር፡"* ተስፋፍቶ ስለተሠራጨው፡ ሰብኣዊና ባዕድ ስለኾነው አሠራር፡ ላቀረብኸው ጥያቄ፡ በኪናውያንና በኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ መልሱ፡ እንደተለመደው፡ ቀላልና ግልጽ ኾኖ፡ እነሆ ቀርቧል። እርሱም፡ እንዲህ ነው፡-

በቅድሚያ፡ በነፍስ አስተሳሰብ፥ በሥጋ አመለካከትና በመንፈስ ተመስጦ እየታየና እየተገመገመ እንደሚወሰነው፡ እንደማንኛውም ዓይነት ጽንሰ አሳብ፥ ወይም፡ ተግባራዊ አሠራር እና/ወይም ሚዛናዊ ፍርድ ኹሉ፡ ይህንም፡ "የወሊድ መቆጣጠሪያን" ምንነትና ማንነት፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ ተመሥርቶ፥ ተገድግዶና ተደምድሞ፡ በሕያውነት በቆመው፡ በእያንዳንዳቸው የተፈጥሮ አካላዊና ባሕርያዊ ሰውነታቸው ውስጥ ባለው፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታቸውና ምግባራቸው፥ ሥርዓታቸውና ህልውናቸው መነጽር፡ ጠልቀው ይመለከቱታል፤ ይመረምሩታል።

ቀጥሎ፡ በኃይለኛውና በረቂቁ የመንፈስ ቅዱስ እሳት ምድጃቸው፡ አቅልጠውና አንጥረው በማውጣት፥ ፍጹም ፍትሓዊና ርትዐዊ በኾነው መለኮታዊ የፍርድ ሚዛናቸውም አጣርተው፡ እውነተኛ ገጽታውን በማቅረብ፡ የእያንዳንዳቸውን ውሳኔ፡ በእየራሳቸው ይሰጣሉ።

ይህ፡ "የወሊድ መቆጣጠሪያ" ነገር፡ እንደዓለማውያኑ ጉዳዮችና የአሠራር ልማድ፡ በማኅበር፥ በጉባኤ፥ በድምፅ ብልጫ የሚወሰን አይደለም። እግዚአብሔር፡ እንደማንኛውም መመሪያው፥ እንደማንኛውም፡ ሥርዓቱና እንደማንኛውም፡ እውቀቱ ኹሉ፡ ይህን፡ "የወሊድ መቆጣጠሪያ" ነገርንም በሚመለከት፡ በእየአንዳንዱ ሰብኣዊ ፍጡሩ ልቦና ውስጥ፡ ግልጽ አድርጎ፡ በቃሉና በእጁ የጻፈው፡ መመሪያው፥ ሥርዓቱና እውቀቱ አለ።

ታዲያ! በየልቦናችን ሰሌዳ ላይ ተጽፎ የምናየውና የምናነብበው፡ ያ መለኮታዊ መመሪያው፥ ያ መለኮታዊ ሥርዓቱ፥ ያ መለኮታዊ እውቀቱ፡ ለእያንዳንዳችን፡ ምን ይለናል? መልሱ፡ እዚያው፡ በአንተም፥ በእኔም፡ በሌሎቻችንም ልቦና ላይ፡ በጉልህና በግዙፍ ተጽፎ፡ በግልጽ የምናየውና የምናነብበው ስለኾነ፡ እኔ፡ ለምን እጠየቃለሁ? አንተስ፡ እኔን፡ እንዴት፡ ትጠይቀኛለህ?

እስኪ፡ ይህንኑ መልስ፡ ዐብረን እንየው! ዐብረንም እንመርምረው! ለእኛ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ይህንና ይህን የመሰለውን ጉዳይ፡ ምንነቱንና ማንነቱን ለይተን በምናውቅበት፡ ከላይ በተገለጠውና ፍቱን መሣሪያችን በኾነው፡ በቅዱሱ ኪዳን መነጽራችን፥ መመርመሪያችንና መመዘኛችን፡ "ይህ፡ 'የወሊድ መቆጣጠሪያ' ነገር፡ ከቶ ምንድር ነው? የእግዚአብሔር፥ ከእግዚአብሔርና ለእግዚአብሔር ነወይ?" ብለን፡ ለእየራሳችን ለምናቀርበው ጥያቄ፡ የምናገኘው መልስ፡ ምን ይኾናል?

ለዚህ ጥያቄ፡ የሚስሰጠው መልስ፡ "ይህ፡ 'የወሊድ መቆጣጠሪያ'፡ ጽንሰ ሓሳብ፡ በሌላው፡ የእግዚአብሔር በኾነው ሥራ ላይ እየደረሰና እየተደረገ እንደሚታየው ኹሉ፡ ከሃይማኖት ጉድለት የተነሣ የመጣ ስለኾነ፡ የእግዚአብሔር፥ ከእግዚአብሔርና ለእግዚአብሔር አይደለም!" በሚል አጭር የድምዳሜ ቃል ተጠቃልሎ ይገለጻል።

"ጕድለቱ ደረሰበት!" የተባለውም ሃይማኖት፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ ተመሥርቶና ከእርሱ መንጭቶ፡ በእግዚአብሔራዊው እውነትና እውቀት፥ እምነትና ሕይወት፡ ንጽሕናና ቅድስና፥ ግልጽነትና ፍጹምነት፡ እነሆ፡ ለ፯ሺ፭፻፮ (ሰባት ሺህ አምስት መቶ ስድስት) ዓመታት፡ በሕያውነትና በዘለዓለማዊነት ሲፈስስ የኖረውና የሚኖረው፥ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትም የምትመራበት፡ የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን ነው።

"ይህ፡ የወሊድ መቆጣጠሪያ ነገር፡ የእግዚአብሔር፥ ከእግዚአብሔርና ለእግዚአብሔር ካልኾነ፡ ታዲያ! የማነው? መልሱ፡ "የዚያ፡ 'እባብ፥ ዘንዶ፥ ሰይጣን፥ ክፉ መንፈስ' የተባለው፡ የዲያብሎስ ነዋ!" የሚል ይኾናል።

ይህ እውነታ፡ የአብርሃም ልጅ የይስሓቅ ልጅ የያዕቆብ ልጅ የኾነው ይሁዳ፡ የወለዳቸው ወንዶች ልጆቹ፡ የሩካቤ ሥጋ ዘራቸውን፡ እንደ"ወሊድ መቆጣጠሪያ"፡ በሴት ማሕፀን ማድረግን "እምቢ!" ብለው፥ በምድር ላይ በማፍሰሳቸው፡ "ይህ ግብራቸው፡ በእግዚአብሔር ዘንድ፡ ክፉ እንደኾነባቸው፥ ከዚህ የተነሣም፡ እነርሱ፡ በሞት እንደተቀሠፉ"፥ ደግሞም፡ ከዚያ ቀደም ብሎ፡ በሰዶምና ገሞራ ሰዎች ዘንድ እንደታየው፡ ዛሬም፡ በ"ወሊድ መቆጣጠሪያው" እንደሚፈጸመው፡ ከተፈጥሮ ሥርዓት ውጪ የሚደረገው፡ የተመሳሳይ ጾታዎች የግብረ ሥጋ ግንኙነት ኃጢኣታቸው፡ በእግዚአብሔር ዘንድ፡ እጅግ በዝቶና ከብዶ፡ ጽዋውም ሞልቶ ስለፈሰሰ፡ እነዚያን ከተሞች፡ በእሳትና ዲን ተቃጥለው እንደተደመሰሱ፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ቃል ተመዝግቦ ይነበባል። (ዘፍጥ. ፲፰፥ ፲፮-፴፫፤ ፲፱፥ ፩-፳፱፤ ፴፰፥ ፩-፴።)

ኹሉን ለመልካም የፈጠረው፥ እኛም፡ በዚህ ማንነቱ ያመንነው እግዚአብሔር እኮ፡ "በአዳምነታችሁ፡ በመልኬ ፈጠርኋችሁ! በሥላሴነቴም፡ ከእኛ እንደአንዱ አደረግኋችሁ!" ያላቸውን፡ የመጀመሪያዎቹን ሰዎች፡ በወንድነት እና በሴትነት ጾታዎች፡ ለኹለት ከከፈላቸው በኋላ፡ እንደገና፡ በጋብቻ አንድነት አዋሕዶ፡ መሰሎቻቸው የኾኑትን፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆችን በመውለድ፡ እንዲባዙ ያደረገው፡ ለመልካም መኾኑን እናውቃለን።

ታዲያ! ይህን እውነታ ካወቅንና ካመንበት በኋላ፡ እንዴት፡ "የወሊድ መቆጣጠሪያ" የተባለውን፡ ይህን የእግዚአብሔርን መልካም ፈቃድ የሚቃረን፡ ሰይጣናዊ ተግባር እንፈጽማለን? እንኳንስ፡ በተግባር ልንፈጽመው፡ አስበን ልናቅደውም አይገባንም።

በመሠረቱ፡ ያንን ክፉ ተግባር፡ አስበንና ዐቅደን የምንፈጽመው፡ ካለማወቅ የተነሣ አይደለም፤ የእግዚአብሔር አብ መልኩ የኾነችው ነፍሳችን፡ መልካሙን የእግዚአብሔርን የሥነ ፍጥረት ሥርዓት፡ ኾነ ብላ፡ በመፃረር፡ ያንን ክፉ ተግባር፡ አስባና ዐቅዳ፡ በሥጋዊው አካሏና ባሕርይዋ የምትፈጽመው ነው። አዎን! የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የኾነውና "ከእኛ እንደአንዱ ኾነች!" ያሰኛት መንፈሳዊው አካሏና ባሕርይዋ፡ የእግዚአብሔር ወልድ ክፍል በኾነው፡ በሥጋዊው የአካል እስትንፋሷና የባሕርይ ቃሏ መሣሪያነት ሳይቀር፡ አበክሮና አጠንክሮ የተናገራትን እኮ፡ ነፍስ፡ ሰምታ ከመቀበልና ከመፈጸም፡ "እምቢ" ብላ ነው።

"እምቢ" ያለችውም፡ መንፈሳዊው አካሏና ባሕርይዋ፡ ያን ፍጹም እውቀት ከገለጠላት በኋላ፡ አኹንም፡ ከነፍሳዊው የሃይማኖቷ ጉድለትና ከሥጋዊው የምግባሯ ድክመት የተነሣ፡ እርሱን፡ "አሻፈረኝ!" ብላ፡ በክህደት፥ በዓመፅና በአምልኮ አመንዝረኛነቷ የምትቀጥል በመኾኗ ነው።

ነፍሳችን፡ ምርጫዋ፡ እግዚአብሔርን የመምሰሉን ብቅዓት የምታገኝበትን፡ መንፈስ ቅዱሳዊውን አካሏንና ባሕርይዋን የኾነ እንደኾነ ግን፡ እግዚአብሔር፡ በመልካምነት የፈጠረውን፡ ማናቸውንም ነገርና የሠራውን ሥርዓት ኹሉ፡ መልካም መኾኑን በማመን፡ በመልካምነት የተፈጠረውን የውስጥ ባሕርያዊ ስሜቷን ጭምር፡ በመንፈስ ቅዱሳዊው የሃይማኖት ኃይል እየተቈጣጠረች ትፈጽማለች እንጂ፡ የፈጣሪዋን ፈቃድ የምትቃወም አትኾንም፤ አዎን! የእግዚአብሔር የኾነውን መልካሙን ነገርና ሥርዓት ለማፍረስ በሚሞክርና ፀረ እግዚአብሔር በኾነ፡ ክፉ ሥራ ላይ የምትሰማራ አትኾንም። እዚህ ላይ፡ ያ፡ "ክፉ ግብር"፡ የምንነጋገርበት፡ "የወሊድ መቆጣጠሪያ" የተባለው ርእስ ነገር ነው።

በዚህ አንጻር፡ ነፍሳችን፡ "የወሊድ መቆጣጠሪያ" በተባለው ክፉ ግብር ተጠምዳ፡ የቀንበሩ ተሸካሚና የልማዱ ባሪያ የምትኾነው፡ ምርጫዋ፡ እግዚአብሔርን ከሚያስመስላት፡ ከመንፈስ ቅዱሳዊው አካሏና ባሕርይዋ ውጪ አድርጎ፡ ሰይጣንን የሚያስመስላትንና ለእንስሳዊው ፍላጎቷ ተገዢነት የሚዳርጋትን፡ የሥጋዊ አካሏንና ባሕርይዋን ፈቃድ ፈጻሚ ስትኾን ነው።

በዚህ ረገድ፡ የእግዚአብሔር የኾነው፡ መልካሙ ነገርና ተፈጥሮአዊዉ ሥርዓት ምንድር ነው? "የወሊድ መቆጣጠር" የተባለውንስ፡ ተፃራሪና ሓሳዊ ነገር፡ ምን አመጣው? እንዲህ፡ አስፈላጊ ሊኾን የቻለበት መነሻ ምክንያትስ፡ ከቶ ምንድር ነው? ለእነዚህ ጥያቄዎች፡ መልስ የኾነውን ቍም ነገር፡ እስኪ፡ በአጭር ሓተታም ቢኾን፡ እናብራራው!

## ቅዱሱ ኪዳን፡
## ስለወንድ ዘር እና ስለሴት ወርኀዊ አበባ የሚለው።

ከላይ፡ ቀደም ብሎ እንደተወሳው፡ የእግዚአብሔር የተፈጥሮ ሥርዓት የኾነው፡ የወንድና የሴት፡ የሩካቤ ሥጋ ፍትወት [የሥጋ ግንኙነት ፍላጎት]፡ መልካም እንጂ ክፉ፥ ቅዱስ እንጂ፡ ርኩስ አይደለም። አካሉና ባሕርዩ፡ በመሠረቱ፡ እንዲህ፡ በፍጹም መልካምነትና ቅድስና፡ ውበትንና ንጽሕናን የተቀዳጀ፥ መነሻ ምንጩና መድረሻ ግቡም፡ በፈጣሪ አካላዊ መልክና ባሕርያዊ ጠባይ፡ በመለኮታዊ ሥነ ጥበብ የተከናወነ፡ ሰብአዊ ፍጡርን የሚያስገኝ ነው።

እውነታው፡ ይህ ኾኖ ሣለ፡ ይህ ኹሉ፡ ያማረና የጸዳ፡ ዕፁብ ድንቅ የመለኮት ሥራ፡ ከዚህ፡ ከእግዚአብሔራዊው የእውነት ምንነቱና ማንነቱ፡ ፈጽሞ ተቀይሮ፡ በዚያ፡ በክፋቱ ኃይል፡ "ኃጢአት" የሚል የርኵሰት ስያሜ ተሰጥቶት፡ እንዴት፡ ወደሰይጣናዊው የሓሰት ምንነቱና ማንነቱ እንደተለወጠ መመልከቱ፡ እጅግ ያሳፍራል፤ ያስተክዛልም።

ይኸውም፡ ቅዱሱ ፈጣሪ፡ በተቀደሰው የሥነ ፍጥረት ትንግርታዊ ጥበቡ፡ ፍጹም ቅዱስና መልካም አድርጎ የፈጠረውን አካልና የሠራውን ሥርዓት ተከትሎ፡ በተባዕቱና በእንስቲቱ፥ ማለትም፡ በወንዱና በሴቲቱ ሰውነት ውስጥ በሚነሣሣው ባሕርያዊ ፍትወት ምክንያት፡ ከወንዱ ጾታዊ አካል የሚፈልቀው ዘር፡ እንደአንዳች ክፉ ነገር ተቆጥሮ፡ እንዴት፡ ራሱ፡ "ኃጢአት!" እንደተባለ፥ ዘሩን ለመቀበል፡ ከሴቲቱ ጾታዊ አካል የሚፈልቀው፡ የወር አበባም፡ እንዴት፡ "መርገም! ርኵሰት!" እንደተባለ፥ ደግሞም፡ የወንዱ አባለ ዘር፥ የሴቲቱም ማሕፀን፡ ኹለቱም፡ "ኀፍረተ ሥጋ!" የሚል የመታወቂያ ስያሜ ተሰጥቷቸው፡ እንዴት፡ እግዚአብሔራዊውን የክብር ማዕርጋቸውን ተገፍፈው፡ ወደሰይጣናዊው የውርደት ዐዘቅት ሊጣሉ መቻላቸው ነው።

ይህ ይትበሃል፡ እግዚአብሔር፡ በንጽሓ ጠባይ፡ በመልኩ በፈጠረውና "ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!" ባለው ሰውነት ውስጥ፡ "ኃጢአትን ጨምሮ ነው የሠራው!" አያሰኝምን? እንዲህ እንዳይባልማ፡ ማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር፡ ሰውን ለአምላክነት ባበቃው፡ በጥንተ ተፈጥሮው ንጽሓ ጠባይ ጸንቶና ያን መርጦ እስከቀጠለ ድረስ፡ ክፋት፥ ኃጢአትና ሞት ሊቀርቡት በማይቻላቸው፡ እግዚአብሔርን በሚመስልበት ሕይወት ይኖራል፤ እንደኄኖክና እንደቅድስት ድንግል ማርያም፥ እነርሱንም እንደመሰሉት ቅዱሳንና ቅዱሳት ማለት ነው።

ይህም እውነታ፡ ጥንት፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ እንደተረጋገጠው፥ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያትም አምነውበት፡ ሲከተሉትና ሲፈጽሙት በኖሩበት ሕይወት ገዝፎ ታይቷል።

ነገር ግን፡ ማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር፡ እንደጸታው ዓይነት፡ ለዓቅመ አዳም ሲደርስ፥ ወይም፡ ለዓቅመ ሔዋን ስትደርስ፡ የግል ምርጫው፡ ይህ፡ የጽድቁ፡ ማለትም፡ የእግዚአብሔሩ እውነት፡ መኾኑ ቀርቶ፡ ከዚህ ይልቅ፡ የኃጢአቱ፡ ማለትም፡ የዲያብሎሱ ሓሰት፡ በሚኾንበት ጊዜ፡ "ኃጢአተኛ"፡ ማለትም፡ "የእግዚአብሔርን እውነት ያጣ፡ ሓሰተኛ!" ተብሎ፥ሰውን ለአምላክነት ያበቃውንና በጥንተ ተፈጥሮው የተቀዳጀውን፡ ያን ንጽሓ ጠባይ ተገፍፎ፥ የክፋት፥ የኃጢአትና የሞት ባሪያም ኾኖ፡ ዲያብሎስን በሚመስልበት ህልውና ይኖራል።

እግዚአብሔር፡ በንጽሓ ጠባይ፡ በመልኩ በፈጠረውና "ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!" ባለው ሰውነት ውስጥ፡ ኃጢአትን ጨምሮ እንደፈጠረ የሚያስመስለውን፡ ይህን እኩይና መሠሪ ነገር፡ በጽሙና ሲያስቡትና በተመስጦ ሲመረምሩት፡ እጅግ እያስገረመ፡ ሥጋውዊ ብቻ ሳይኾን፤ ነፍሳዊውንና መንፈሳዊውን ጭምር አጠቃልሎ፡ የሰዎች፡ የመመልከቻ ዓይኖቻቸው፡ የቱን ያህል እንደታወሩ፥ የማወቂያ አእምሮዎቻቸውም፡ የቱን ያህል እንደደነዘዙ፥ የማስተዋል ኅሊናዎቻቸውም፡ የቱን ያህል እንደማሰኑ፡ ለመገመትም እንኳ ያዳግታል። ይልቁንም፡ "የእግዚአብሔር ወገኖችና አገልጋዮች፥ ተጠሪዎቹም ነን!" በሚሉት ዘንድ፡ የክፋቱ አበጋዝ የኾነው ዲያብሎስ፡ የቱን ያህል እንደሠለጠነ፡ በገሃድ የሚያረጋግጥ ማስረጃን ያስጨብጣል።

በእግዚአብሔር መልክ በተፈጠረው፥ ፈጣሪውም፡ "ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!" ባለው፡ በሰብአዊው ፍጡር ሰውነት ውስጥ፡ በሥላሴ የተዋሕዶ ምሥጢር፡ አንድ የኾኑት፡ የነፍስ፥ የሥጋና የመንፈስ፡ ሦስቱም አካላትና ባሕርያት፡ በራሱ፡ በእግዚአብሔር የተፈጠሩ፥ ከእርሱ የተገኙና የእርሱ የኾኑ መኾናቸው፡ በሥነ ፍጥረትም ኾነ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን የተረጋገጠ እውነት ነው።

እውነታው፡ ይህ ከኾነ፡ ታዲያ! ከእግዚአብሔር አብ ባሕርይ ተከፍላ፡ የተፈጠረችው ነፍስ፡ ከንጽሓ ልቡና አካሏና ባሕርይዋ የሠረፀውን፥ በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረውን፥ ፈጣሪውም፡ "ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!" ያለውን፡ ሰብአዊ ፍጡር ለማስገኘት የሚያስችላትን፡ የሩካቤ ሥጋ ፍትወቷን ለመፈጸም፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በኾነው፡ በመንፈሳዊው አካሏና ባሕርይዋ ስምምነት፥ የእግዚአብሔር ወልድ በኾነው፡ በሥጋዊው አካሏና ባሕርይዋ ዘር አማካይነት የምታካኺደው፡ እግዚአብሔራዊው የተፈጥሮ ሥርዓት፡ የተቀደሰው ረቂቁ ስሜትና ቅዱሱ ዘር ጭምር፡ "ጽድቅ" መኾኑ ቀርቶ፡ እንዴት፡ "ኃጢአት" ተብሎ ይሰየማል፤ "ቅድስና" መኾኑ ቀርቶስ፡ እንዴት፡ "በኃጢአትነት" ይፈረጃል?

ቀደም ብሎ፡ ተደጋግሞ እንደተገለጸው፡ ይህ ኹሉ ሓሳዊ ሙከራ፡ ሊደረግ ቀርቶ፡ ፈጽሞ ሊታሰብም የሚገባው አይደለም፤ ሰይጣናዊ ነውና።

ኃጢአትስ፡ በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረውን፥ ፈጣሪውም፡ "ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!" ያለውን፡ ሰብኣዊ ፍጡር እንዲያስገኝ፡ እግዚአብሔር የሠራውን፡ ይህን፡ የተቀደሰ፡ ዕፁብ ድንቅ ሥርዓት፡ "ኃጢአት ነው!" ብሎ፡ "በኃጢአትነት" መፈረጅ ነው።

ኃጢአትስ፡ እግዚአብሔር፡ ለዚሁ ቅዱስ ዓላማው፡ ከግብ መድረስ፡ በዚሁ ሰብኣዊ አካልና ባሕርይ ውስጥ፡ በንጽሓ ጠባይ፡ ቀድሶና አንጽቶ፥ አስውቦና አጣፍጦ የፈጠረውን ዘርና የወር አበባ፡ "ኃጢአትና መርገም፥ ርኵሰትና አደፍ" ብሎ ማንቋሸሽና መስደብ ነው።

ኃጢአትስ፡ እግዚአብሔር፡ በጥንተ ተፈጥሮ፡ "ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!" ብሎ፡ በመልኩ ለፈጠረው ሰብኣዊ ፍጡሩ፡ መልካም የደስታ ሕይወት ይኾንለት ዘንድ የሠራለት ሥርዓትና የሥርዓቱ አባላት፡ "ኃጢአት ናቸው!" ብሎ፡ በዚያ ሰውነት ውስጥ፡ የሌለ ስሜታዊ ጭራቅንና ምትሓታዊ ደዌን በማሳደር፡ ያን ሰው፡ ለማያቋርጥ ፍርሃትና ድንጋጤ፥ ጭንቀትና ሥጋት መዳረግ ነው።

ኃጢአትስ፡ በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረውን፥ ፈጣሪውም፡ "ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!" ያለውን፡ ሰብኣዊ ፍጡር ያስገኙ ዘንድ፡ እግዚአብሔር የሠራውን፡ የተፈጥሮ ሥርዓት፡ "ኃጢአት ነው!" ብሎ፡ በኃጢአትነት በመፈረጅ፡ የሰው ወገኖች ኹሉ፡ ያን እግዚአብሔራዊ የኾነውን የተፈጥሮ ሥርዓት ተከትለው፡ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነታቸውን፡ ከፍትወት ተባባሪያቸው፡ ማለትም፡ ወንድ፡ ከሴት፥ ሴትም፡ ከወንድ ጋር ከማድረግ ይልቅ፡ "የወሊድ መቆጣጠር" ጠንቅን ያስከተለውንና ከጾታ መሰሎች ጋር፡ ግብረ ሰዶምን፡ በይፋና በሕጋዊነት እስከማካኼድ የሚያደርሰውን፡ ኢተፈጥሮአዊ፡ ማለትም፡ ከተፈጥሮ ውጪ የኾነውን፥ እንስሳት፥ አራዊትና አዕዋፉት እንኳ የማያደርጉትን አስጸያፊ ነውር መፈጸም ነው።

ከዚህ ኹሉ ኹኔታ የምናገኘው፡ አንድ አስተማማኝ ነገር አለ፤ ይኸም፡ እግዚአብሔር የፈጠረው ነገር ኹሉ፡ መልካምና የተቀደሰ ኾኖ ሣለ፥ ይህንም፡ ራሷ፡ ሥነ ፍጥረት ጭምር የምታረጋግጠው ኾኖ ሣለ፥ ከዚህ የተነሣም፡ ይኸው እውነታ፡ "ጽድቅ"፡ ወይም፡ "እውነት" ተብሎ፡ በፍጥረተ ዓለሙ ዘንድ ተቀባይነትን አግኝቶ ሊሰፍን የሚገባው፡ እርሱ ኾኖ ሣለ፥ እውን ኾኖ ያለው እውነታም፡ ይህ ኾኖ ሣለ፥ ይኼ ኹሉ ቀርቶ፡ ህልውና የሌለውና ዲያብሎስ፡ በክፋትና በርኵሰት የጠነሰሰው "ሐሰት"፡ ስሙንና መልኩን ቀይሮ፡ "ኃጢአት" ተብሎ፥ የእውነታውንም ቦታ ይዞ፡ እንዲህ መግነኑና ማየሉ፡ የሰዎች ክፉ አስተሳሰብ፡ እንዴት፡ እውነቱን፡ ሐሰት፡ ማለትም፡ ጽድቁን፡ ኃጢአት ማድረግን እንደሚችል ነው።

# ቅዱሱ ኪዳን፡
# በምትሓታዊው የኃጢአት ቀንበር ለሚሠቃዩ፡ ያለው ምክር።

እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር፡ ከፈጣሪው ቍጥጥር ሳይወጣ፡ የእርሱ መሣሪያ ኾኖ፡ የእርሱን የተቀደሰ ዓላማ ከማገልገል፡ ራሱን ሊያገለል እንደማይችል ይታወቃል፤ ለዚህም፡ በቀዳማዊው የሥጋ ፅንሰቱና ልደቱ፡ ወደዚህ ዓለም ያደረገው አመጣጡ፥ በምድራዊ ዕድገቱና ኑሮውም ረገድ፡ በዚሁ፡ በተወለደበት ዓለም ውስጥ የሚያካኼደው ቆይታው፥ በመጨረሻው የሞት ጽዋውም፡ ከዚህ ዓለም፡ ተጠርቶ የመኼዱ ገሃድ ኹኔታ፡ በቂ ማስረጃ ነው።

እንደሰንሰለት የተያያዘው፡ ይህ ኹሉ የህልውና ኺደት፡ በዚያ ሰብአዊ ፍጡር ላይ በሚደርስበት ጊዜ ግን፡ በመልካሙና በክፉው፥ በእውነቱና በሓሰቱ፥ በሕይወቱና በሞቱ ረገድ፡ ያ ሰብአዊ ፍጡር፡ የሚፈልገውን ለማድረግ፡ አካላዊና ባሕርያዊ ኾኖ፡ ከፈጣሪው የተለገሠው፡ ፍጹሙ የእውቀት ጸጋ፥ የመምረጡ ነጻነትና የመወሰኑ ሥልጣን፥ የማድረጉም ኃይል፡ የተጠበቀለት መኾኑ እንዳይዘነጋ ያስፈልጋል።

አኹንም፡ እውነታው፡ ይህ ከኾነ፡ ታዲያ! ያው ሰብአዊ ፍጡር፡ በእግዚአብሔር በኩል የሌለውንና ያልተፈጠረውን፥ ነገር ግን፡ ክፉውን አስተሳሰብ፡ ራሱ፡ በውስጡ በማፍለቅ፥ የዲያብሎስንም መንገድ በመከተል፡ ለምን፡ ራሱን፡ ለማያስፈልግ ጭንቀትና ችግር ዳረገ? ለምንስ ይዳርጋል? የዚህ ጭንቀትና ችግር ሰለባ ከመኾን የደረሰውም እኮ፡ በአፍአዊ አካሉና በውሳጣዊው ባሕርዩ በኩል፡ ከየራሱ ሰብኣዊና ተፈጥሮአዊ፥ ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ዓቅም በላይ፥ ከቍጥጥሩም ውጭ ኾነው ለሚያገኟቸው፥ ከራሱ ለሚመነጩና የራሱ ከኾኑት ኃይላት ጋር፡ ትግልንና ግጭትን በመፍጠሩ እንደኾነ፡ ግልጽ ነው።

እያንዳንዱ ሰው፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ ይህንና ሌላውንም የችግር ዓይነት፡ በእየራሱ ላይ የሚያመጣው እኮ፡ ከላይ፡ ተደጋግሞ እንደተብራራው፡ ፈጣሪው፡ በተፈጥሮ፡ በውስጡ ባስቀመጣቸው፡ እርሱን፡ እግዚአብሔርን በሚያስመስሉት፡ የነፍስና የሥጋ፥ የመንፈስም አካላትና ባሕርያት አማካይነት፡ የራሱ አድርጎ የሰጠውን እውቀትና በእነርሱ አማካይነት የሚነግረውን ቃል ንቆና ትቶ፡ ከውጭ፡ ሌሎቹ፡ የፍጥረት ተጋሪዎቹ የኾኑት መሰሎቹ ፍጡራን፡ ማለትም፡ በሥጋ ያሉት ሰዎችና በመንፈስ ያሉት ሰይጣናት የሚሉትን ብቻ፡ አውቆም ኾነ ሳያውቅ፡ በዕውርነት ስለሚከተል ነው።

ከዚህ ችግር ለመውጣት፡ ያው ሰው፡ ይኼን የተሳሳተ አካኼዱን፡ ጨርሶ አቁሞ፡ እውነቱንና መልካሙን ወደሚያስታውቀውና ወደሚመራው፡ ወደእግዚአብሔራዊው የተፈጥሮ ምንነቱና ማንነቱ፡ በፍጹም ንስሓ፡ መመለስ አለበት። በዚህ ጊዜ፡ እግዚአብሔር፡ ጥንቱኑ፡ መልካምና እውን አድርጎ የፈጠረው፡ ደግነትንና እውነትን፥ ሕይወትንም እንጂ፡ መጥፎና ባዶ የኾኑትን፡ ክፋትንና "ኃጢአት" የተባለውን፡ ሓሰትን፥ ሞትንም አለመኾኑን ያውቃል።

አዎን! እነዚህን፡ የሌሉ ምትሓቶች የኾኑትን፡ ክፋትንና "ኃጢአት" የተባለውን፡ ሓሰትን፥ ሞትንም፡ በተፃራሪ አስተሳሰባቸው፡ እንዳሉ አድርገው አምጥተው፡ በሌሎች ደካሞች ፍጡራን ዘንድ፡ ተቀባይነትና ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው፥ ከዚህ የተነሣም፡ በፍጥረተ ዓለማቱ ላይ፡ እንዲህ፡ የማያቋርጥ ችግርና ሁከት እንዲደርስ ያደረጉት፡ ከመናፍስቱ መካከል፡ የመጀመሪያው ፍጡር፡ ዲያብሎስ ሲኾን፡ ከሰዎች መካከል ደግሞ፡ የመጀመሪያዋ ሴት፡ ሔዋን ናት።

ከዚያን ጊዜ አንሥቶ፡ እግዚአብሔር ያልፈጠረውና ራሱ፡ "ሓሰት" የኾነው ኃጢአት፡ ይኸው፡ እንደምናየው፡ በ"ወሊድ መቆጣጠር" ስም ሳይቀር፡ በሰዎች፡ የግል፥ የቤተሰብና የኅብረተሰብ ህልውናና ሕይወት ላይ፡ የቱን ያህል፡ ከባድና የተወሳሰበ የኾነ ችግርን ፈጥሮ፡ የሰዎችን ምድራዊ ኑሮ፡ እንዴት እንዳቃወሰና በሥቃይ እንዳማሰነ እንመለከታለን።

ስለዚህ፡ ከዚህ የሌለና የማያስፈልግ ችግርና ሥቃይ ለመውጣት፡ እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር፡ ሴትም ኾነች ወንድ፡ ቆራጥ የኾነ፡ የምርጫ ውሳኔን፡ ያለአንዳች መዘግየት፡ ማድረግ ያስፈልገዋል። ይኸውም፡ እየራስን፡ የእግዚአብሔር በኾነውና በእየራስ ሰውነት ውስጥ በሚገኘው፡ የተፈጥሮ እውቀትና በእውነተኛ ንስሓ፡ ለቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖትና ምግባር፥ ሥርዓትና ሕይወት ማብቃት ነው።

ወደዚህ ብቅዓት የሚያደርሰው ዝክረ ነገርና መመሪያ፡ ባለፈው ዓመት፡ በነሓሴ ፲፮ ቀን፥ ፳፻፲ ዓመተ ምሕረት፡ ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በይፋ በተላለፈው፡ ቍጥር ፩/፳፻፲ ዐዋጅ እና ከእርሱ በፊት፡ "ለታላቁ ቃለ ዐዋዲ፡ ቀዳሚ መልእክት" በሚል ርእስ፡ በወጣው መግለጫ ውስጥ ይገኛልና፡ እነዚህኑ መመልከት የሚጠቅም ይኾናል።

ይህ ሳይኾን ቢቀር ግን፡ ሌላው ምርጫ፡ አኹን ባለው፡ የችግርና የሥቃይ ህልውና፡ በባሰ ኹኔታ መቀጠል ብቻ ይኾናል።

ከዚህ ይልቅ፡ ከላይ በቀረበው ጥሪ መሠረት፡ እየራስን፡ የእግዚአብሔር በኾነውና በእየራስ ሰውነት ውስጥ በሚገኘው፡ የተፈጥሮ እውቀትና በእውነተኛ ንስሓ፡ ለቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖትና ምግባር፥ ሥርዓትና ሕይወት ለማብቃት ከተቻለ፡ በዚህ ጊዜ፡ እነዚያ፡ የፀረ እግዚአብሔር ኃይላት፡ ሳይኖሩ እንዳሉ አድርገው የፈጠሯቸው፡ ክፋት፥ "ኃጢአት" የተባለው፡ ሓሰትና ሞት ተወግደው፡ በዚህ ምድራዊ ዓለም፡ በሥጋ ህልውናው ሕያው ኾኖ በሚንቀሳቀሰው፡ በዚያ ኪዳናዊ ሰውነት ውስጥ፡ የእግዚአብሔር የኾኑት፡ መልካምነትና ደግነት፥ እውነትና ሕይወት ብቻ ይሰፍናሉ።

ከዚህ በኋላ፡ "የወሊድ መቆጣጠርን" እና ከእርሱ ጋር የተያያዙትን፡ የሩካቤ ሥጋ ፍትወትን፥ የወንድን ዘርና የሴትን የወር አበባ፥ ሌሎችንም ተመሳሳይ ርእሶችን በማጠቃለል፡ ከራስ የሰውነት አካልና ባሕርይ ጀምሮ የሚሠርፀውና የሚስሰማው፥ የሚታሰበውና የሚታየው፥ የሚኾነውና የሚፈጸመው ኹሉ፡ በኃጢአት መልኩና ይዘቱ መኾኑ ቀርቶ፡ በእግዚአብሔራዊው ቅድስናና ንጽሕና ብቻ ይኾናል።

ከዚያ በኋላ፡ በዚያ ኪዳናዊ፥ ወይም፡ ኪዳናዊት ሰውነት ውስጥ የሚሠርፀው አሳብና በአንደበት የሚነገረው ቃል፡ እንዲህ የሚል ይኾናል፡-

"እንግዴህ ወዲህ፡ ክፋትና "ኃጢአት" የተባለው ሓሰት፥ ሞትም፡ በእኔ ላይ ሥልጣን የላቸውም! የእነርሱ ተገዥ ከኾንሁበት ህልውና፡ ነጻ ወጥቻለሁ! ዛሬ፡ እኔ፡ በኪዳናዊ/በኪዳናዊት ኢትዮጵያዊነቴ፡ የምኖረው ሕይወት፥ የምኾነውና የማስበው፥ የምናገረውና የማደርገው ኹሉ፡ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነትን ጨምሮ፡ በጋብቻ ምክንያት፡ "ጽድቅ" እንጂ፡ "ኃጢአት"፥ "ቅድስና እንጂ፡ "ርኵሰት" አይደለም። ነገር ግን፡ በውስጤ ያለው የመንፈስ ቅዱስ የኾነው ባሕርዬ፡ ማለትም፡ ኅሊናዬ፡ "ይህን ልታደርግ፡ አይገባም!" ብሎ የሚነግረኝን፡ አላደርገውም።

"ምናልባት፡ ይህንኑ፡ "ልታደርገው አይገባም!" ተብሎ የተነገረኝን ጥፋት፡ ከጋብቻ ውጪ የኾነ፡ የተፈጥሮ የግብረ ሥጋ ግንኙነትም ቢኾን፡ ከዓቅሜ በላይ በኾነ፡ አንዳች ኃይልና ምክንያት ተገድጄ፥ እንዲያውም፡ አውቄም እንኳ የማደርገው ቢኾን፡ በልቶና ጠጥቶ፡ እንደመጸዳዳቱ የተፈጥሮ ግዳጅ እንደተካኼደ ቈጥሬ፡ እፈጽመው ይኾናል እንጂ፡ "ኃጢአት" መኾኑን አምኜ አላደርገውም፤ አለዚያ፡ ገና፡ የኃጢአት ቀንበር ተሸካሚ መኾኔን ማመን ይኾንብኛልና።

"እውነታው ግን፡ ኃጢአት፡ በእኔ ላይ ሥልጣን ስለሌለው፥ እርሱዉም፡ ከድንግል ማርያም በተወለደው፡ በእግዚአብሔር ልጅ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት ባገኘሁት ንስሓዬ፥ ቀደም ብሎም፡ "ወነአምን በአሓቲ ጥምቀት፡ ለስርየተ ኃጢአት!" ማለትም፡ "ኃጢአት በሚሰረይባት፡ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን!" በምትለው ሃይማኖቴ፡ ለአንዴና ለዘለዓለም ስለተሰረየልኝ፡ ከኃጢአት ነጻ በኾነው፡ በዚያው የቅድስናና የንጽሕና ሕይወቴ እቀጥላለሁ እንጂ፡ ባለማወቅ፡ የእርሱ ተገዢ ኾኜ ስሠቃይ ወደቆየሁበት የባርነት ኑሮዬ፡ ፈጽሞ አልመለስም።

"በሰውነቴ የተፈጥሮ አካላትና ባሕርያት ግፊት፡ ምናልባት፡ አኹንም፡ ከዓቅሜ በላይ በኾነ ኃይልና ምክንያት፡ ተገድጄም ኾነ አውቄ፡ የፈጸምሁት ያ፡ የቀደመው የጥፋት ድርጊቴ ቢደጋገምም፡ አኹንም፡ ራሴን፡ ከዚያ፡ የቅድስናና የንጽሕና ሕይወቴ ላለማውጣትና ተመልሼ የኃጢአት ቀንበር ተሸካሚ ላለመኾን፡ በዚያው መጠን፡ በሚደጋገመው ንስሓዬ አማካይነት፡ ራሴን እያጸዳሁ እቀጥላለሁ እንጂ፡ በምንም ኹኔታ፡ በኃጢአት ኃይል ተሸንፌ፡ ራሴን፡ ለክፋትና ለሞት፡ ከቶ አልሰጥም።

"አዎን! 'ወንድሜ፡ ቢበድለኝ፡ ስንት ጊዜ ይቅር ልበለው? ሰባት ጊዜን?' ብሎ፡ ሓዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ላቀረበለት ጥያቄ፡ 'የለም! እስከሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ፡ እስከሰባት ብቻ አልልህም!" ሲል፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰጠው የተትረፈረፈ የምሕረት ቸርነቱ ተጠቅሜ፡ መልካሙን ኪዳናዊ ሕይወቴን፡ በጽድቅና በንጽሕና ነጻነቴ እቀጥላለሁ።" (ማቴ. ፲፰፥ ፳፩-፳፪።)

እንግዴህ፡ ይኼ ነው፡ በዚህ፡ በተነሣንበት ርእሰ ጉዳይ ረገድ ያለው፡ የአንድ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ እና የአንዲት የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊት እውነተኛነትና ታማኝነት፥ ቆራጥነትና ጀግንነት ተለይቶ የሚታወቀውና ጠርቶ የሚገለጥበት ሃይማኖታዊ ምግባር።

ስለዚህ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ለዚሁ ብሎ፡ ሰው ኾኖና በመስቀል ላይ፡ ቅዱስ ሥጋውን በመቍረስና ክቡር ደሙን በማፍሰስ፡ ይህን በሚያህልና ይህን በሚመስል መሥዋዕትነት ባስወገደው፡ "ኀጢኣት" በተባለው የሌለ ጭራቅ ቀንበር ሥር ወድቃችሁ፡ በእርሱ ጠንቅ የምትማቅቁ ኹሉ አይዟችሁ! በምሥራቹ ቃል ደስ ብሏችሁ፡ ተጠናከሩ! በሌለው የኀጢኣት ጦር፡ የቱንም ያህል ተወግታችሁና ተሸንፋችሁ የቆሰላችሁ መስሎ ቢታያችሁ፡ ኹልጊዜም፡ በንስሓ፡ እንደገና፡ ፍጹም ጤና መኾንና ከወደቁበት መነሣት አለና፡ "ኀጢኣት" ከተባለው ሓሳዊ ቀንበር፡ እየራሳችሁን፡ ነጻ አውጡ!

ኀጢኣት፡ የለም እንጂ፡ እናንተ፡ "አለ!" ካላችሁ፡ እርሱ ይፍራችሁ፥ ይሸሻችሁ እንጂ፡ እናንተ አትፍሩት! ደፍሮ፡ በሓሳዊ ምትሓትነቱ፡ ወደእናንተ እንደመጣባችሁ ካሰባችሁም፡ በእግዚአብሔር መልካምነትና እውነት፥ ቅድስናና ንጽሕና በሚያምነው መንፈሳችሁ ኾናችሁ፡ "በእኔ ዘንድ ያለው፡ የእግዚአብሔር ጽድቅ እንጂ፡ አንተ አይደለህም። አንተማ የለህም። ስለዚህ፡ አንተ ሰይጣን! ከፊቴ ወግድ!" ብላችሁ፡ በአሸናፊነት ተጋፈጡት! ተቋቋሙት! አስወግዱትም!

ከዚህ በኋላ፡ በዚህ መንፈስ ቅዱሳዊ አቋም ኾናችሁ፡ ያን፡ እርሱ፡ በኀጢኣትነት የመጣበትን ግብር፡ ከዓቅማችሁ በላይ በኾነ፡ በተፈጥሮአዊው ፍትወተ ሥጋችሁ ተገፋፍታችሁ ብትፈጽሙት እንኳ፡ ይህ፡ ግዳጅ፡ መልካሙ የእግዚአብሔር ዕቅድ ሊፈጸምበት የመጣ፡ "ጽድቅ እና ቅድስና ነው!" ብላችሁ ተቀበሉት እንጂ፡ "ኀጢኣትና ርኵሰት ነው!" አትበሉት። ምናልባት ግን፡ በዚህ ድርጊታችሁ፡ ጥፋተኝነትና በደለኛነት ቢሰማችሁ፡ ወዲያው፥ እዚያው፡ በእውነተኛ ንስሓችሁ አስወግዱት።

የእግዚአብሔር እውነት፡ በዚህ ረገድ፡ ለእናንተ እየተናገረች ያለችው፡ ይኼ ቃል፡ ስለኀጢኣት ብቻ ሳይኾን፡ ስለግብረ አበሮቹ፡ ስለክፋትና ስለሞትም ጭምር ስለኾነ፡ ያ፡ የእግዚአብሔር የእውነት ቃል፡ በእነዚህም ላይ የጸናና የሚጸና መኾኑ ሊታወቅ ይገባል።

# ቅዱሱ ኪዳን፡
# ስለጋብቻና ስለሩካቤ ሥጋ፡ ለትውልዱ የሚለው።

በዚህ ረገድ፡ በተለይ፡ አኹን የተነሣንበትን፡ "የወሊድ መቆጣጠርን" በሚመለከት፡ በተለይ፡ የዘመኑ ሰብአዊ ትውልድ፡ ለምን ወደዚህ የማያስፈልግ ችግር ውስጥ እንደተዘፈቀ እንመልከት!

በመጀመሪያ ነገር፡ ኹለቱም ጾታዎች፥ ወይም፡ አንዳቸው፡ የሩካቤ ሥጋ ፍትወታቸውን ተቆጣጥረው መግታት የማይችሉ ከኾኑ፡ ይህንኑ ፍትወት፡ በመልካምነትና ለመልካሙ ሕያው ዓላማ የፈጠረው ፈጣሪ፡ ለዚህ ችግር፡ ቀላልና ተገቢ የኾነውንም፡ መልካም መፍትሔ፡ ዐብሮ ፈጥሮ፡ የአፈጻጸሙን ሥርዓት ጭምር አደላድሎ የሠራ መኾኑን ማወቅ ነው። ያም የመፍትሔ ሥርዓት፡ <u>ጋብቻ</u> ነው።

ጋብቻን ላለመፈጸም፡ በተለይ፡ በዛሬው ዘመን፡ የሚቀርቡ፡ ሥፍር ቍጥር የሌላቸው ምክንያቶችና ሰበቦች ሊኖሩ ይችላሉ። ነገር ግን፡ እነዚህ ምክንያቶችና ሰበቦች፡ የቱንም ያህል በርካታና ከባዶች መስለው ቢታዩም፡ ጋብቻ በተቀመጠበት በሌላው የሚዛኑ ቍና ላይ ሠፍረው፡ የእግዚአብሔር ሥርዓት የኾነውን፡ እርሱን፡ ጋብቻን፡ በክብደታቸው ሊደፉት፡ ከቶ አይቻላቸውም። መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ **"ከሕግ፡ አንዲት ነጥብ ከምትወድቅ፡ ሰማይና ምድር ቢያልፍ ይቀላል።"** ያለው መለኮታዊ ቃል፤ እዚህ ላይ የሚጸና መኾኑን ማስተዋል ነው። (ሉቃ. ፲፮፥ ፲፯።)

ጋብቻ፡ "አያስፈልገኝም!" በማለት፡ ለመነኰሳቱም ያልተቻለውን፡ ከእርሱ፡ ጨርሶ ለመገለል ቀርቶ፤ ተፈጥሮአዊ ምልክቱ የኾነው፡ የፍላጎቱ ዕድሜ ከሚጠይቀው በላይ፡ እርሱን፡ ጋብቻን ለማዘግየት መሞከሩ እንኳ፡ ከዚህ መለኮታዊ የማስጠንቀቂያ ቃል ነጻ አያደርግም። **"አታመንዝር"** የሚለውን፡ ከዐሥሩ የእግዚአብሔር ቃላት፡ አንዱ የኾነውን፡ ሃይማኖታዊ ምግባር፡ አክብሮ ለመጠበቅና ለመፈጸም፡ በጋብቻ መወሰን ያስፈልጋል፤ ይገባልም፤ ሌላ ማማረጫ የለም።

እዚህ ላይ፡ ከዐሥሩ የእግዚአብሔር ቃላት መካከል፡ አንዱ የኾነው፡ "አታመንዝር!" የሚለው ርእሰ-አንቀጽ፡ ያለጋብቻና ከጋብቻ ውጪ ከሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ጋር አግባብነት ስላለው፡ በዚህ ረገድ፡ የቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን፡ ምን እንደሚል፡ ጥቂት ማስረዳት አስፈላጊ ይኾናል።

"አመንዝራነት"፡ ወረተኛነት ነው፤ ማለትም፡ በአንድ ጸንቶ አለመርጋት ነው። ለዝሙት ብቻ ሳይኾን፡ ለሌሎች ግብሮች፥ በተለይና በይበልጥ፡ ለአምልኮም ይውላል። አንዱን ፈጣሪ እግዚአብሔርን ማምለክን ትቶ፡ ሌላ፡ ጣዖትን፡ ማለትም፡ ሕያዋን ፍጡራን የኾኑትን መናፍስትንና ሰዎችን፥ በድን የኾነ ቅርፅን ብቻ ሳይኾን፡ ገንዘብን ጨምሮ፡ ሥጋዊ የኾነውን፡ ሀብትን፥ እውቀትንና ሥልጣንን፡ አምላክ አድርጎ፡ ለዚያ መስገድ ወይም መገዛት፡ አመንዝራነት ነው።

የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ "የእግዚአብሔር ሥርዓት ነው!" ብለው አምነውበት እየፈጸሙ የኖሩትና የሚኖሩት ጋብቻ፡ እንደአዳምና ሔዋን፡ በእግዚአብሔር መንግሥት፡ እስከሞትና ከዚያም በኋላ በሚጸና አንድነት፡ ህልውናን፡ በሕያውነት መቀጠል ነው።

በዚህ አንጻር፡ በተቃራኒነት ያለው አመንዝራነት ግን፡ ይህን፡ እግዚአብሔራዊ ሥርዓት ትቶ፡ የተቀደሰውን ጋብቻ፡ ኹለቱም ባልና ሚስት፥ ወይም አንዳቸው፡ በፈለጉ ጊዜ፡ እያፈረሱትና፡ እየለዋወጡት፥ እነርሱም፡ እየተፋቱና ከሌላው ጋር ሌላ ጋብቻን እየመሠረቱ፡ ባለመጽናትና በወረት መኖር ነው፤ "እሥራኤል ነን!" የሚሉት፡ አይሁድ እንደሚያደርጉት ማለት ነው።

ይኸው፡ ከእግዚአብሔር ሥርዓት፡ የወጣው፡ የጋብቻ ሕጋቸው ብልሹ መኾኑን፡ በግልጽ በማስታወቅ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ነቅፎባቸው፡ አመንዝራነት፡ ጋብቻን ማፍረስ መኾኑን፡ እንዲህ በሚለው፡ መለኮታዊ ቃሉ አረጋግጧል፦ "**ያለዝሙት ምክንያት፡ ሚስቱን ፈትቶ፡ ሌላዪቱን የሚያገባ ኹሉ፡ ያመነዝራል፤ የተፈታችውንም የሚያገባ፡ ያመነዝራል።**" (ማቴ. ፲፱፥ ፫-፲፫።)

ስለዚህ፡ ጋብቻን አጽንቶ፡ ከጋብቻ ውጪ የሚደረግ ሩካቤ ሥጋ፡ ዝሙት ሲኾን፡ ራሱን ጋብቻን ማፍረስ ግን፡ "አታመንዝር!" ያለውን፡ ከአሥሩ፡ የእግዚአብሔር ቋሚ ቃላት፡ አንዱ የኾነውን፡ መተላለፍ እንደኾነ፡ ከላይ የተጠቀሰው፡ የጌታ ቃል፡ በሚበቃ ያስረዳል። ለልዑል እግዚአብሔር እና ለዚህ ኹሉ በደል ቤዛ የኾነ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ለወለደች፡ ለድንግል ማርያምም ምስጋና ይድረሳቸውና፡ እነዚህ፡ ኹለቱም ዓይነት "ኃጢአቶች"፡ በንስሓ የሚነጹና የሚስተካከሉ ኾነዋል።

እግዚአብሔር፡ "ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!" ብሎ፡ በመልኩ የፈጠረውን ሰው እንዲያስገኝለት፡ የሠራውን፡ ጋብቻንና ሥርዓቱን፡ ሕያውና ጤናማ አድርጎ ለማቆየት፡ የሚፈጽመውን ትንግርት መመልከት ነው፤ ከእነዚህ መካከል፡ አግባብነት ያላቸውን፡ አንዳንዶቹን፡ እዚህ ላይ መጥቀሱ፡ አስፈላጊ ይኾናል። ለምሳሌ፡ የጋብቻው ፍላጎት፡ አለመቀነሱ፡ አንዱ ትንግርት ሲኾን፥ በእርሱ አማካይነት፡ የሚፀነሱትና የሚወለዱት ወንዶችና ሴቶች ብዛት፡ ምንጊዜም ተመጣጣኝ ኾኖ መቀጠሉ፡ ሌላው ትንግርት ነው።

በዚህ መልክና ይዘት፡ በጋብቻ የቃል ኪዳን ሥርዓት የሚኖሩ ባለትዳሮች፡ ምናልባት፡ ከኹለቱ፡ በአንዳቸው፥ ወይም፡ በኹለቱም ላይ፡ የጤንነት ጉድለትንና የሕይወት ማጣትን ጠንቅ የሚያስከትልባቸው ካልኾነ በቀር፥ ለዚህም ችግር፡ ሃይማኖታዊ የኾነውን መፍትሔ ለማግኘት፡ ባልና ሚስቱ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ፡ የባሕርይ ሕይወቱ የኾነውን፡ መንፈስ ቅዱስን በመካከላቸው፡ ሦስተኛ አባል አድርገው፡ ኹለቱም፡ በስምምነት የሚመካከሩበት ካልኾነ በቀር፡ "የወሊድ መቆጣጠር" በተባለው ክፉ ወጥመድ ውስጥ፡ ራሳቸውን ማጠላለፍ የለባቸውም።

የዚህንም ምክንያት፡ ማብራራት ቢያስፈልግ፡ እርሱን፡ እንደሚከተለው ማቅረብ ይቻላል። በመጀመሪያ ነገር፡ እኒህ ኹለት ባለትዳሮች፡ በሃይማኖታቸውና በምግባራቸው፥ በኑሮ ሥርዓታቸውና በሕይወታቸው፡ በቅድሚያ፡ እየራሳቸውን፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ያበቁ፥ ጋብቻቸውንም፡ በዚሁ መሠረት የፈጸሙ፥ ወይም፡ ያስተካከሉ መኾን ይኖርባቸዋል። ከዚህ በኋላ፡ የባለትዳሮቹ ዕድል፡ ያለአንዳች ጭንቀትና ሥጋት፥ ያለምንም ችግርና ሁከት፡ በፍጹሟ የእግዚአብሔር ነጻነትና ፍቅር፥ ደስታና ሰላም፡ ዘለዓለማዊቷን፡ የትንሣኤና የሰንበት ሕይወትን፡ በፍጹሚ፡ የነፍስ፥ የሥጋና የመንፈስ ዕረፍት መኖር ብቻ ነው።

የተቀደሰው ጋብቻቸው፡ እንዲህ የተፈጸምው፥ እኒህ ኪዳናዊ ባል እና ኪዳናዊት ሚስት፡ መኻታቸው፡ የተቀደሰ ኾኖ፡ በማናቸውም ጊዜ፡ ተስማምተውና ተፈቃቅደው በሚፈጽሙት ሩካቤ ሥጋቸው፡ ረክተውና ተደስተው፡ የትዳር ህልውናቸውን፡ ይህን ኹሉ መልካም ስጦታን ላበረከተላቸው፡ ለቸሩ ፈጣሪያቸውና ለቅድስት ድንግል እናቱ፡ የማያቋርጥ ምስጋናቸውን በማበርከት ይቀጥላሉ።

እኒህ የቃል ኪዳን ባለትዳሮች፡ መልካሙን ሕይወታቸውን፡ እንዲህ በሚኖሩበት ጊዜ፡ ይህንኑ፡ መልካሙን ኑሮአቸውን፡ በእግዚአብሔር ምስጋናና በሰብአዊ እርካታ ከመቀጠል በቀር፡ ልጆችን ስለመውለድ፥ እነርሱም፡ ወንዶች፥ ወይም፡ ሴቶች ስለመኾናቸው፥ ስንት መኾን እንዳለባቸውም፥ እነርሱንም፡ መቼ፥ መፅነስና መውለድ እንዳለባቸው፥ እነዚህንና እነዚህን ስለመሰሉት የተያያዙ ጉዳዮች፡ የሚያስቡትና የሚያቅዱት፥ የሚሠጉበትና የሚጨነቁበትም፡ ምንም ነገር ከቶ የለም።

ይኼማ፡ የእነርሱ ጉዳይ ሳይኾን፡ የእርሱ የፈጣሪያቸውና የቃል ኪዳን አምላካቸው፡ መለኮታዊና ሥልጣናዊ የኃላፊነት ድርሻ ነው፤ ይህንም እውነታ፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታቸው አማካይነት ያገኙት፥ ያመኑበትና የሚኖሩት እግዚአብሔራዊው እውቀት፡ በትክክልና በአጽንዖት አረጋግጦ አስገንዝቧቸዋል። በዚህ እግዚአብሔራዊ እውቀታቸው መሠረት፡ ኪዳናዊው ባልና ኪዳናዊት ሚስት፡ የቱንም ያህል የበዛ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ቢያደርጉም፡ ከወንድ አብራክ ወጥቶ፡ በሴት ማሕፀን የሚያርፈውን፡ የተባዕቱን ዘር፡ በመለኮታዊ ፈቃዱና ጥበቡ፡ በእንስቲቱ ወርኃዊ ደም አማካይነት፡ በእግዚአብሔር መልክና "ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!" ለተባለው ለሰውነት ፅንስና ሽልነት የሚያበቃው፡ እግዚአብሔር ብቻ መኾኑን፡ አበክረው ያውቃሉ።

በዚህ ዓይነት፡ እልፍ አእላፋቱን ከያዘው፡ ከወንዱ የዘር ቋት መካከል፡ እርሱ፡ እግዚአብሔር ብቻ በሚያውቀው ምሥጢራዊ ጥበቡ፡ ከእርሱ፡ ከእግዚአብሔር ተከፍላ፡ በዚያ ማሕፀን ውስጥ ከምትገኘው፡ ከነባቢቷ፥ ለባዊቷና ሕያውቷ ነፍስ ጋር፡ በሴቲቱ ማሕፀን ውስጥ፡ ከደሟ ጋር ተዋሕዶ፡ ለዚያ፡ የሰውነት ፍሬ የሚበቃው፡ የትኛው፡ አንዱ፥ ወይም፡ ኹለቱ፥ ወይም፡ ከዚያም በላይ፡ ስንቱ ዘር እንደኾነ፥ ያም፡ በጾታው፡ ወንድ፥ ወይም፤ ሴት እንዲኾን የሚያደርገው፥ ጽንሱም፡ መቼ ሊኾን እንደሚገባው፡ የሚያውቀውና የሚወስነው፥ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

በአጠቃላይም፡ በምድር ላይ፡ ሰውን ጨምሮ፡ ምን ያህል የፍጥረት ወገን ሊኖር እንደሚገባ፡ መጥኖ ማስተካከል የሚቻለው፥ ለዚህም ኹሉ ክዋኔ፡ ከውጥኑ አንሥቶ፡ እስከፍጻሜው፡ መብቱና ችሎታው፥ ሥልጣኑና ኃይሉ ያለው፡ እርሱ፡ የፍጥረተ ዓለማቱ ፈጣሪና ባለቤት የኾነው፡ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

በተፈጥሮ ሥርዓቱ፡ መንፈሳዊውን ቅድስናና ሥጋዊውን ንጽሕና ጠብቀውና ተከትለው ከሚፈጽሙ በቀር፡ አዎን! በዚህ ክንውን ውስጥ፡ ከውጥኑ አንሥቶ፡ እስከፍጻሜው ድረስ፡ ባልና ሚስቱን የሚያገባቸው፡ አንዳችም ተሳታፊነት፡ ፈጽሞ የለም። በዚህ ረገድ፡ ለእነርሱ የሚኾነውን፡ የቸርነቱን ሥራ የሚያደርግ፡ እርሱ እግዚአብሔር መኾኑን፡ እነርሱም ያውቃሉ።

ይኹን እንጂ፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ በኹሉም አግጣጫ እንደሚታየው፡ ሰዎች፡ የእግዚአብሔርን ትተው፡ የራሳቸውን ስሑት መንገድ በሚከተሉበት ጊዜ፡ የሚደርሰው ኹናቴ፡ ይኸው ዛሬ፡ በእውነተኛዪቱ ሃይማኖት ጉድለት የተነሣ፡ "የወሊድ መቆጣጠርን" እና በእርሱ ጠንቅ፡ በሰዎች ላይ እየደረሰ ያለውን ጽኑና ቀሣፊ፥ ታላላቅና የተለያዩ የኾኑ ችግሮችን የመሰለው መኾኑን፡ እነሆ፡ ኹሉም፡ በገሃድ የሚመለከተው ነው።

የባልና ሚስቱ ድርሻ፡ የልዑል እግዚአብሔርና የቅድስት ድንግል ማርያም ልጆች የመኾናቸውን ጸጋ ለመቀበል፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ክህነታዊ ንጉሥነትና በእናቱ አገራዊ ንግሥትነት በምትመራው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ደግሞ፡ ነጋሢዎች የመኾናቸውን ክብር ለመቀዳጀት፥ በመጨረሻም፡ ይህችኑ፡ መለኮታዊት መንግሥትና መሪዎቿን፡ የሚያገለግሉ ካህናት የመኾናቸውን ሢመት ለመጐናጸፍ የበቁባትን፡ የቅዱሱ ኪዳን፡ ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታቸውንና ምግባራዊ ሥርዓታቸውን፡ በፍጹም ታማኝነት ጠብቀውና ፈጽመው መኖር ብቻ መኾኑን፡ ኹለቱም ባለትዳሮች ያውቃሉ።

በእነርሱ በኩል ይህን ድርሻቸውን ጠንቅቀው ከፈጸሙ፡ ሰውኛው "የወሊድ መቆጣጠሪያ"፡ "ሊያደርግ ይችላል!" ተብሎ የሚታሰበውን ብቻ ሳይኾን፡ ከማይታሰበውም በላይ፡ ለእነርሱ፡ ምድራዊና ዘለዓለማዊ ሕይወት፡ የሚበጃቸውንና የሚጠቅማቸውን ትንግርት፡ በቅዱሱ ኪዳን ያመኑበትና የተማመኑበት፡ ቸሩ ፈጣሪያቸው፥ ቅድስት ድንግል እናቱም፡ ፈጽመውላቸው ያገኙታል።

## ቅዱሱ ኪዳን፡
## ስለጋብቻ መሠረታዊ ዓላማ የሚለው።

በሥነ ፍጥረት ሥርዓት፡ በወንድ እና በሴትነት ጾታ ተለይቶ የተከሠተው፡ እግዚአብሔራዊው የጋብቻ ዓላማ፡ መሠረታዊ ግቡ፡ "መውለድ"፥ "መዋለድ" መኾኑን፡ በኦሪት ዘፍጥረት፡ ምዕራፍ ፩፥ ቍጥር ከ፳፯ እስከ፳፰ ላይ ተጽፎ የሚነበበው፡ "ብዝኁ! ወተባዝኁ! ወምልዕዋ ለምድር።" ማለትም፡ "ብዙ! ተባዙ! ምድርንም ሙሏት!" የሚለው ቃል፡ አረጋግጦ ያመለክታል።

በዚህ ረገድ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ለዝንተ ዓለም፥ ማለትም፡ እንግዴህ፡ ለ፯ሺ፭፻፪ ዓመታት፡ ጠብቀውትና አክብረውት፥ ተከትለውትና አጽንተውት ሲፈጽሙት የኖሩት፡ የባልና ሚስት የጋብቻና የመኻታ፡ እርሱም፡ የሩካቤ ሥጋ ዝክረ ነገር፡ ይህን የሚመስል እንደኾነ፡ ከላይ የሠፈረው ሓተታ፡ በሚበቃ ያስረዳል።

እርሱንም፡ እዚህ ላይ፡ እንዲህ በሚል፡ አጭር ቃል አጠቃልሎ ማቅረብ ይቻላል፡-

እግዚአብሔር፡ በአዳም እና በሔዋን የመሠረተውና የጀመረው፥ እስከዛሬና አኹን፥ ወደፊትም እየኾነና እየተፈጸመ የሚቀጥለው፡ እውነተኛውና የሚጸናው ጋብቻ፡ ይህ ነው፡- እርሱ እግዚአብሔር ብቻውን ባወቀ፥ እነርሱ፡ ወንድዬውና ሴቲቱ ግን፡ በማያውቁት፥ ሊያውቁትም በማይቻላቸው መንገድ ተገናኝተውና ተዋውቀው፡ ከተዋደዱና ከተፈቃቀዱ፥ በፍጹም ፍቅርና ስምምነትም፡ በእግዚአብሔር ስምና በመንፈስ ቅዱስ እማኝነት፡ ለጋብቻ፡ ቃል ኪዳናቸውን ካደረጉ፡ "በቃ! እግዚአብሔር፡ በአዳም እና በሔዋን የመሠረተውና የጀመረው፡ እውነተኛው ጋብቻ ተፈጸመ፣ የጸናም ኾነ!" ይባላል።

በዚህ ጊዜ፡ በብሉይ ኪዳኑ የተነገረውና በአዲስ ኪዳኑ የጸደቀው፡ እንዲህ የሚለው የእግዚአብሔር ቃል እውን ይኾናል፡- "ዘፈጠሮሙ እግዚአብሔር እምትካት፡ ተባዕተ፥ ወአንስተ ገብሮሙ፤ ...እንከሰኬ፡ ኢኮኑ ክልኤተ፤ አላ አሐዱ ሥጋ እሙንቱ፤ ዘእግዚአብሔር አስተፃመረ፡ ሰብእ ኢይፍልጥ።" ማለትም፡ "በመጀመሪያ፡ እግዚአብሔር፡ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፤ ...እንግዴህ፡ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ፡ ኹለት አይደሉም። ስለዚህ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አንድ ያደረገውን፡ ሰው አይለየው!"

ይህ ነው፡ የእግዚአብሔር ሥርዓት። ይህ፡ የእግዚአብሔር ሥርዓት፡ በመንፈስ ቅዱስ ተወጥኖና ተከናውኖ የሚፈጸም ስለኾነ፡ ሰውኛውና ሰይጣናዊው የዐውደ ነገሥቱና የልማዱ፥ የአማጩና የሽማግሌው፡ የውሉና የጽሑፍ ኪዳኑ፥ የሕጉና የሃይማኖቱ ውጣ ውረድና ግርግር ፈጽሞ አያስፈልገውም።

ከዚህ በኋላ፡ እኒህ፡ የአባታቸው፡ የእግዚአብሔር እና የእናታቸው የድንግል ማርያም ሙሽሮች፡ ሩካቤ ሥጋን ለመፈጸም እስከመፈለግ የሚያደርስ ፍላጎት ከተነሣሣባቸው፥ ያንንም ከፈጸሙትና ከዚያ፡ ሩካቤ ሥጋ፡ ሰው ከተፀነሰ፡ ያ ጋብቻቸው፥ ያ መኻታቸውና ሩካቤ ሥጋቸው፡ በእግዚአብሔር የተቀደሰና የተባረከ፡ ፍሬያማ መኾኑ ታወቀ፥ ተረዳ፥ ተረጋገጠ! ማለት ነው። ከዚህ በኃላ፡ በባልና ሚስትነት ትዳራቸው፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕይወታቸውን፡ በይፋ መቀጠል ነው።

ይኸው እግዚአብሔራዊው ሥርዓት፡ ከጋብቻው ጀምሮ፡ በሩካቤ ሥጋው አልፎ፡ እስከልጅ መውለዱ ድረስ፥ በአጠቃላይ፡ የትዳሩ ቤተሰባዊ ኑሮ፡ እንከን የሌለበት፡ ፍጹም መኾኑ የሚረጋገጠው፡ ለአካለ መጠን፥ ይኸውም፡ ለዓቅመ አዳምና ለዓቅመ ሔዋን የሚደርሱበትን ዕድሜያቸውን ጠብቀው፡ በቅዱሱ ኪዳን ከተጋቡ በኋላ፡ በዚህ ሕይወት የሚኖሩት ኪዳናውያኑ ኢትዮጵያውያንና ኪዳናውያቱ ኢትዮጵያውያት፡ የቱንም ያህል የበዙ ልጆችን ቢወልዱ፡ በዚያ፡ ቤተሰብ ውስጥ፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ ፍላጎታቸው በኩል፡ ምንም የሚጎድላቸው ነገር ሳይኖር፡ በኹሉም አግጣጫ፡ የሚገኘው መለኮታው ጸጋ፡ የተሟላ መኾኑ ነው።

ይኸውም፡ እጅግ ተትረፍርፎ፡ ከሚታየው፡ የእግዚአብሔር በረከት በስተቀር፡ በእነዚያ፡ ጤናማና ሕያዋን ኾነው፡ በመልካም በሚያድጉት፥ ለዓቅመ አዳምና ለዓቅመ ሔዋን ዕድሜ ደርሰው፡ ለቍም ነገር በሚበቁት፥ በዘመናችንም መሥፈርት፡ እጅግ በርካታ በኾኑት ልጆቻቸው ምክንያት፡ ለዛሬው፡ ለተነሣንበት፡ "ለወሊድ መቆጣጠር" መንሥኤ ይኾናሉ የሚባሉት ችግሮች ኹሉ፡ ፈጽመው አለመኖራቸው ነው።

በአኹኑ ዘመን ሲካኼድና ሲፈጸም እንደሚታየው፡ ይህን እግዚአብሔራዊዉን ሥርዓት፡ በማቃለልና በማግለል፥ እንዲያውም፡ በመናቅና በማስወገድ፡ ነገር ግን፡ ለሰውኛውና ለሰይጣናዊዉ እውቀትና ፈሊጥ፡ ቅድሚያንና ብልጫን በመስጠት፡ በእርሱ ቦታ፡ የአሕዛብና የባዕዳን የኾነውን፡ "የወሊድ መቆጣጠር"ን ጨምሮ፡ ሌላውን መተካት፡ ነፍሳዊውንና መንፈሳዊውን መልካም ህልውና ብቻ ሳይኾን፡ ሥጋዊውንና ምድራዊዉን ሳይቀር፡ ማጣት መኾኑ፡ ይኸው፡ በእውን እየታየ ባለውና እየጨመረ በሚኼደው ችግር ማረጋገጥ ይቻላል።

እዚህ ላይ፡ ተያይዞ ሊወሳ የሚገባው ተጨማሪ ቍም ነገር አለ፤ እርሱም፡ እንደሚከተለው ተገልጾ ቀርቧል፦

ምናልባት፡ እየራሳችሁን፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ የጋብቻ ሕይወት ገና ያላበቃችሁ፡ አካለ መጠን ያደረሳችሁ፡ ወንዶችም፥ ሴቶችም፡ በብዛት እንዳላችሁ ይታመናል። በዚህ ጽሑፍ አማካይነት፡ ለእናንተም፡ የምናስተላልፈው መልእክት፡ ከላይ እንደተጠቀሰው፡ እየራሳችሁን፡ ለዚሁ፡ ለቅዱሱ ኪዳን፡ ኢትዮጵያዊ የጋብቻ ሕይወት እንድታበቁ ነው። እስከዚያው ድረስ ግን፡ ይህንኑ፡ የ"ወሊድ መቆጣጠሩ"ን ግብር በሚመለከት፡ ከዚህ በላይ ከተገለጸው እውነታ ጋር፡ በተጨማሪ ልታውቁት የሚገባውን ቍም ነገር እናክልላችኋለን።

ጋብቻን እስክትፈጽሙ ድረስ፡ በዕድሜያችሁ፡ አካለ መጠን ያደረሳችሁ ደናግል፡ ወንዶችም፥ ሴቶችም፡ ከሌላው የጾታ ባልደረባችሁ ጋር፡ ሩካቤ ሥጋ ታደርጉ ዘንድ፡ የፍትወተ ሥጋችሁ ፈቃድ፡ እንደሚነሣሣባችሁ ይታወቃል። በዚህ ጊዜ፡ ይህ፡ የፍትወተ ሥጋችሁ ፈቃድ፡ የኃጢአት ስሜት መስኂችሁ፡ በውስጣችሁ ሁከት እንዳይፈጠርባችሁ መጠንቀቅ ይኖርባችኋል።

በውስጣችሁ የተነሣሣባችሁ፡ ይህ፡ የፍትወተ ሥጋችሁ ፈቃድ፡ እግዚአብሔራዊ የኾነው፡ መልካሙ የተፈጥሮ ጸጋ ስለኾነ፡ ደስ ብሏችሁ ተቀብላችሁት፡ በአግባቡ፡ ልታስተናግዱት ይገባችኋል። ምግብ በማየት፥ ወይም፡ በረሃብ ምክንያት፡ በውስጣችሁ የሚፈጠረው፡ ማናቸውም ዓይነት፡ የመብል፥ ወይም፡ የመጠጥ ፍላጎት፡ ኃጢአት እንዳልኾነ ኹሉ ማለት ነው።

በአግባቡ፡ ልታስተናግዱት የሚገባችሁ፡ እንዴት ነው? በየጊዜውና በየምክንያቱ፡ በውስጣችሁ የሚነሣሣባችሁን፡ ሌላውን፡ ማናቸውንም ዓይነት፡ የሥጋ ፍላጎታችሁን፡ ተቆጣጥራችሁና ገርታችሁ እንደምትቋቋሙትና እንደምታለዝቡት፥ በመጨረሻም፡ እንደምታቸንፉት ማለት ነው። ለምሳሌ፡ ለሥጋዊው ሕይወታችንና ህልውናችን፡ በእጅጉ የሚያስፈልገንን መብልንና መጠጥን፥ ደግሞም፡ እጅግ የምንወድደውን የምግብ፥ ወይም የመጠጥ ዓይነት፡ በጾም ኃይል፡ እንዴት ተቈጣጥረን፡ ነፍስንና መንፈስን ብቻ ሳይኾን፡ ሥጋችንን ጭምር፡ ወደፈለግነው ግብ ለማድረስ እንደምንችል ማለት ነው።

ጣዕም ያለውን መጠጥ የመጠጣት ብርቱ ፍላጎት ቢኖርብንም እንኳ፡ ኃይለኛ የወይን፥ ወይም፡ የማር ጠጅን አብዝተን ከጠጣን፡ እንደምንሰክር ስለምናውቅ፡ ተገቢውን መጠን ጠብቀን፡ በመለኪያ ለመጠጣት፥ እንዲያውም፡ ጨርሶ ላለመጠጣት፥ ይህንም፡ እጅግ ጽኑ የኾነውን፡ የሥጋን ፍትወት (ፍላጎት)፡ በጠንካራው መንፈሳዊ አካልና ባሕርይ ኃይል፡ እንዲህ፡ በዚህ መልክና ይዘት ተቆጣጥሮ፡ መቋቋምና ማሸነፍ ይቻላል። ጥምባሆም፡ የሳምባ ነቀርሳ በሽታን እንደሚያስከትል ስለሚታወቅ፡ የልጅነት ጨቅላነት፥ ወይም፡ የጕርምስና ግለት ቢገፋፋም እንኳ፡ ላለማጤስ መወሰን እንደሚቻል፡ ማለት ነው።

ምናልባት፡ ይህን ኹሉ ተጋድሎ፡ በጾምና በጸሎት፥ በስግደትም ጭምር ፈጽማችሁት፡ አኹንም፡ የሩካቤ ሥጋ ፍላጎታችሁን ነበልባል ለማቀዝቀዝ፥ የማዕበሉንም ኃይል፡ ለማረጋጋት ሳትችሉ ብትቀሩ፡ በመሠረታዊው እግዚአብሔራዊ ተፈጥሮው፡መልካም የኾነው፡ ይህ የጋለና የጸና ስሜታችሁ፡ እንዲህ እየጠነከረ የኼደበት፡ አንዳች የተለየ፡ መንፈስ ቅዱሳዊ ምክንያት እንደሚኖረው መገንዘብ ይኖርባችኋል። ከዚህ በኋላ፡ በዚህ አቋም ኾናችሁ፡ ሩካቤ ሥጋውን፡ ከኃጢአት ስሜት በጸዳ፡ በንጹሕ ፍቅር ለመፈጸም፡ ዒላማ የኾነውን ወገን፡ በቀጥታ ኼዶ፡ ፊት ለፊት በመገናኘት፥ በእግዚአብሔር ስምና እውነት፡ በግልጽ በማነጋገርም፡ ግቡ፡ ጋብቻ የኾነውን ግንኙነት፡ በዚህ ኹኔታ መጀመር ይቻላል።

ይህን የመሰለው የተቀደሰ የጽድቅ ስሜት፡ የቅዱሱ ኪዳን ታማኝ በኾነ ሰውነት ውስጥ በጽናት የሚነሣሣው፡ ያለበቂና ያለመልካም ምክንያት፡ እንዲያው በከንቱ አለመኾኑን መረዳቱ አግባብ ይኾናል። የፍትወቱ ስሜት ፈጣሪ በኾነው፡ በራሱ፤ በእግዚአብሔር ፈቃድ እንደኾነ ማመንም ይገባል።

ይህ ስሜት የተቀሰቀሰውና እየተጠናከረ የኼደው፡ "መጨረሻውና ውጤቱ፡ ሕያው ለኾነ፡ ለአንድ መልካም ዓላማ ነው!" ብሎ፡ በዚያ ታማኝ ኪዳናዊ ሰውነት ውስጥ ያለው መንፈስ ቅዱስ፡ በእርግጥ ያሳስባል፤ ያም፡ ሕያው የኾነው፡ መልካሙና ዘለዓለማዊው ዓላማ፡ ጋብቻ እና/ወይም፡ በእግዚአብሔር መልክ የሚፈጠረውንና "ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!" የሚባለውን ሰብአዊውን አካልና ባሕርይ ለማስገኘት የተዘጋጀው መለኮታዊ ዕቅድ የሚፈጸምበት ግንኙነት መኾኑ ነው።

ለነገሩ እኮ፡ ጥንቱኑም ቢኾን፡ እግዚአብሔርን መስሎና አኽሎ የሚወለደውን፥ ሰውን የሚያህል ሕያው ፍጡር የሚያስገኘውን፡ ያን፡ የፍትወተ ሥጋ ባሕርያዊ ስሜት፥ አካላዊነት ያላቸውን፡ የወንዱን ዘርና የሴቲቱን የወር አበባ ጨምሮ የያዘው፡ የሥነ ፍጥረት ድንቅ ምሥጢር፡ እጅግ የተዋበና የጣፈጠ፡ ንጹሕና ቅዱስ መኾኑ፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታችን መሠረት፡ ተረጋግጦ የታመነ ነው። ከላይ፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጸው፡ ፈጣሪ ራሱ፡ ፍጹም መልካም አድርጎ እንደፈጠረው፡ እንደሌላው ፍጥረት ኹሉ፡ አዎን! <u>ይህም፡ የፍትወተ ሥጋ ባሕርያዊ ስሜት፥ አካላዊነት ያላቸውን፡ የወንዱን ዘርና የሴቲቱን የወር አበባ ጨምሮ የያዘው፡ የሥነ ፍጥረት ድንቅ ምሥጢር፡ እጅግ የተዋበና የጣፈጠ፡ ንጹሕና ቅዱስ ነው።</u>

ይህን፡ በመለኮታዊው የሥነ ፍጥረት ድንቅ ምሥጢር፡ እጅግ የተዋበና የጣፈጠ፡ ንጹሕና ቅዱስ ኾኖ የተሠራውን፡ የፍትወተ ሥጋ ባሕርያዊ ስሜት፡ "ኃጢአት ነው!" ብሎ፡ በኃጢአትነት መፈረጅ፡ ራሱን ሠሪውን እግዚአብሔርን፡ መንቀፍና በሓሰት መወንጀል፥ መስደብም ነው። በዚህ ጊዜ፡ ያ፡ ይህን የመሰለውን ድፍረት የፈጸመው ሰብኣዊ ፍጡር፡ ራሱ ሰይጣን ኾነ ማለት ነው፤ ለዚህ ድርጊቱም፡ እንደጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል፡ በመለኮታዊዋ የፍርድ ቀን፡ መልስ በመስጠት፡ ፍዳውን እንደሚቀበል፡ ሃይማኖታዊው እውነት ያረጋግጣል። (ማቴ ፲፪፥ ፳፬-፴፯።)

ይህም እውነታ፡ እግዚአብሔር የፈጠረውን የእንስሳና የአውሬ፥ የወፍና የዓሣ ዓይነት ኹሉ፡ መልአኩ፡ በራእይ፡ ከሰማይ አውርዶ አቅርቦለት፡ "በል ብላ!" ባለው ጊዜ፡ "ጌታ ሆይ! አይኾንም፤ አንዳች ርኩስ፥ የሚያስጸይፍም፡ ከቶ በልቼ አላውቅምና!" ሲል መልስ በመስጠቱ፡ "እግዚአብሔር ያነጻውን፡ አንተ አታርክሰው!" የሚል ሰማያዊ ግሣጼን፡ ሦስት ጊዜያት በተቀበለው፥ ከዚህም በላይ፡ ቀደም ብሎ፡ በመምህሩ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት፡ ጌታ የመጣበትን የመስቀል መከራ በመቃወሙ፡ በመለኮታዊው አንደበት፡ "አንተ ሰይጣን! ከኋላዬ ወግድ!" ተብሎ በተዘለፈው፡ በሊቀ ሓዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ ተደጋጋሚ ድርጊቶች፡ ተከሥቶ ታይቷል። (የሓዋ. ፲፥ ፱-፲፯። ማቴ. ፲፮፥ ፳፩-፳፫።)

ራሱ፡ "ሓሰት፣ የሓሰትም አባት" መኾኑ፡ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል የተነገረበት፡ ዲያብሎስና የእርሱ ጭፍሮች የኾኑ ክፉዎች ሰዎች፡ ይህን፡ <u>የሩካቤ ሥጋን፡ ባሕርያዊ የፍትወት ስሜት፥</u> ኾን ብለው፡ በሓሰትና በተንኰል፡ "ኃጢኣት ነው!" ብለው፡ በኃጢኣትነት ፈረጁት እንጂ፡ ማንኛውም፡ ሰብኣዊ ፍጡር፡ በተስተካከለ አእምሮው ካስተዋለው እኮ፡ ሃይማኖታዊውን አስተሳሰብ ሳይቀር፡ ወደጐን አስቀምጦ፡ ልማዳዊዉን የተፈጥሮ ሥርዓት ብቻ: እግምት ውስጥ በማስገባት፡ በቀላሉ፡ ከእውነቱ ለመድረስ እንደማያዳግት መገንዘብ ይቻላል።

ይህን ዘይቤ፡ እስኪ፡ እንዲህ በሚል አገላለጽ ላቅርበው! ፍጡር፡ ፈጣሪው እግዚአብሔር፡ በደነገገለት የተፈጥሮ ሥርዓት፡ በሕይወቱና በህልውናው ለመቀጠል ሲል፡ መብሉንና መጠጡን፡ መርጦና መጥኖ ይበላል፤ ይጠጣልም። ይህ፡ የፍጡሩ፡ የመብላትና የመጠጣት ድርጊት፡ መቼም፡ በእውነተኛውም ኾነ በሓሰተኛው ሰው ዘንድ፡ "ኃጢኣት ነው!" ተብሎ፡ በኃጢኣትነት የሚፈረጅ አይደለም። እንደዚሁ ኹሉ፡ ያንኑ፡ የተፈጥሮውን ሥርዓት ተከትሎ፡ በመብሉና በመጠጡ ምክንያት፡ የሚደርስበትን፡ የመጸዳዳት ግዳጅ ይፈጽማል፤ ይህንኑ ግዳጅ በሚፈጽምበት ጊዜ፡ ይኼም ግዳጅ፡ እንደቀደመው ኹሉ፡ በኹሉም ወገኖች ዘንድ፡ "ኃጢኣት ነው!" ተብሎ፡ በኃጢኣትነት እንደማይፈረጅ የታወቀ ነው። እንደእንስሳቱ፥ እንደአራዊቱና እንደአዕዋፋቱ ኹሉ ማለት ነው።

የሰዉ ወገን፡ ከእንስሳቱ፥ ከአራዊቱና ከአዕዋፋቱ የሚለይበት ኹኔታ፡ ይህን፡ እግዚአብሔራዊዉን የተፈጥሮ ሥርዓትና ግዳጅ፡ በእግዚአብሔር መልክ በተፈጠረበትና በመለኮታዊው ቃል፡ "ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!" በተባለበት፡ መንፈስ ቅዱሳዊ የልዕልና አካሉና ባሕርዩ፡ ተቈጣጥሮና አስተካክሎ፡ ለሚጠበቅበት ፍጹምነት ለማብቃት፡ የመቻሉ እውነታ መኾኑን፡ የማያውቅ የለም።

ድንቅ የኾነው፡ የሰውነታችን ሥጋዊ አካልና ባሕርይ፡ እኛ፡ "እንከን የሌለበት፥ ፍጹም ጥሩ ነው!" ብለን፡ አሳምረንና አጣፍጠን ከሠራነው፥ እንዲሁም፡ "ያስፈልገናል!" ብለን፡ ሳስተንና ጣፍጦን ከበላነው መብልና ከጠጣነው መጠጥ ላይ፡ የሚበቃውን ብቻ አስቀርቶ፡ ሌላውን፡ የማያስፈልገውን፡ ለዚያ፡ ለራሱ ሰውነት የሚያስጸይፍ እስከመኾን በደረሰ ኀሰርነት፡ ከሰውነት እንዲወጣ ያደርገዋል።

እዚህ ላይ ሊታወስ የሚገባውና ከዚህ ጋር የተያያዘው ቊም ነገር፡ ለዚያ ፍጡር፡ መልካም ሕይወትና ጤናማ ህልውና መቀጠል፡ ያ የመጸዳዳቱ ግዳጅ፡ በግዴታም ኾነ በውዴታ፡ በአግባቡና በጊዜው መፈጸም እንዳለበት ነው። ሳይፈጸም ቢቀር ግን፡ ውጤቱ፡ በዚያ ፍጡር ላይ፡ ወደሞት የሚያደርስ፡ የጽኑ በሽታን ጠንቅ ሊያስከትልበት እንደሚችል ይታመናል።

እውነታው ይህ ከኾነ፡ የሩካቤ ሥጋ፡ የፍትወት ስሜትስ፥ ከየት መጣ ይባላል? ከነፍሳዊውና ከመንፈሳዊው የተፈጥሮ ባሕርያት ጋር፡ በሥጋዊነቱ፡ ከዚሁ፡ ከመብሉና ከመጠጡ አይደለምን? አዎን! ነው።

ታዲያ! እርሱስ፡ እንደመብሉና እንደመጠጡ የመጸዳዳት ሥርዓታዊ ግዳጅ፡ በከያኒው ፈጣሪ ጥበብ በተዘጋጀለት ባሕርያዊ መገለጫና አካላዊ አባል አማካይነት፡ ከዚያ ሰብአዊ ፍጡር ሰውነት፡ በአግባቡ ሊወጣ አይገባውምን? አያስፈልገውምንስ?

በአግባቡ ሊወጣ እንደሚገባውና እንደሚያስፈልገውማ፡ የተፈጥሮው ሥርዓት፡ በዚህ አስገዳጅ መልኩና ይዘቱ እየመሰከረና እያረጋገጠ ያስገነዝባል። አለዚያ፡ ያ፡ የመጸዳዳቱ ግዳጅ፡ እንዳይፈጸም ቢደረግ፡ በዚያ ሰብአዊ ፍጡር ላይ፡ "እስከሞት ያደርሳል!" ለተባለው፡ የደዌ ጠንቅ እንደሚጋለጥ ኹሉ፡ በዚህም ረገድ፡ የሩካቤ ሥጋው ፍትወት፡ በግድ፡ እንዲገታ ቢደረግ፡ በዚሁ ሰብአዊ ፍጡር ላይ፡ አንዳች፡ የአካልና የባሕርይ፥ የምግባርም ቀውስ፡ መድረሱ ላይቀር ነው። ባልበቁት መነኮሳት ላይ እንደሚታየው፡ ማለት ነው።

እንግዴህ፡ እግዚአብሔራዊ የኾነው፡ ይህ የተፈጥሮ ሥርዓት ነው፡ ከነአካላቱና ባሕርያቱ፥ ምግባሩ ጭምር፡ ባጠቃላይ፡ "ኃጢአት" ተብሎ፡ በኃጢአትነት የተፈረጀውና ሰዎችን ለቀውስና ለሥቃይ ሊዳርግ የቻለው።

ይኸው፡ የመብላቱና የመጠጣቱ፥ ከዚያም፡ የመጸዳዳቱ ተግባርና ግዳጅ፡ እግዚአብሔራዊዉን የተፈጥሮ ሥርዓት ተከትሎ የሚፈጸም በመኾኑ፡ "መልካምና ተገቢ ነው!" ተብሎ፡ በፍጡራኑ ኹሉ ዘንድ፥ በተለይም፡ በሰዎች ዘንድ፡ ልዩ ክብርና ማዕርግ ተሰጥቶት፡ ያለችግር ሲካኼድ ይኖራል።

ጠንቀኛና አጣብቂኝ ችግር ውስጥ የገባው፡ <u>የተፈጥሮ ባሕርይ የኾነው፡ ይህ፡ የሩካቤ ሥጋ ፍትወት</u> ነው። ስለዚህ ጠንቀኛ ችግርም፡ ዘላቂ መፍትሔ የሚኾን፡ ሌላ ማማረጫ የለም። ምንኵስናም እንኳ፡ ማማረጫ ሊኾን አልቻለም። ቢኖርም፡ ይኸው፡ በሰዎች ዘንድ ታስቦ የተሠራው፡ "የወሊድ መቆጣጠር" የተባለው ብቻ ኾኖ መገኘቱ፡ እጅግ ያሳዝናል። ምክንያቱም፡ ሥጋዊው የመጸዳዳት ግዳጅ፡ እስከመጨረሻው ቢከለከል፡ ለዚህ ጭካኔና ግፍ ሰለባ የኾነውን፡ ያን ሰብአዊ ፍጡር የሚጠብቀው፡ ወደሥጋ ሞት የሚያደርሰው አሠቃቂው የሥጋ ደዌ ብቻ ስለሚኾን ነው።

በዚህ አንጻር፡ ክፉውን (ሰይጣናዊዉን) "የወሊድ መቆጣጠር" የመረጠውን ሰብአዊዉን ፍጡር ግን የሚጠብቀው፡ ይኸው፡ አኹን፡ በምድር ላይ፡ እየደረሰበት ያለው፡ ወደሥጋ ሞት የሚያደርሰው፡ አሠቃቂው የሥጋ ደዌ ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥና በተጨማሪ፡ በዘለዓለማዊነት ወደሚቀጥለው፡ ወደነፍሳዊዉና መንፈሳዊው የሞት ፍዳ የሚያደርሰው፡ ሥጋዊው፥ ነፍሳዊውና መንፈሳዊው የፈተና ሥቃይ ነው፤ ይህም፡ በሦስቱም አካላትና ባሕርያት፥ ማለትም፡ በሥጋ፥ በነፍስና በመንፈስ፡ እንደእሳት እያነደደውና እንደማዕበል እያማታው ያለው፡ የፍርሃትና የጥርጣሬ፥ የሥጋትና የጭንቀት መከራው ኾኖ ይገኛል።

## ቅዱሱ ኪዳን፡
## ለምስክርነት የሚያቀርባቸው፡ የአብነት ማስረጃዎች።

እዚህ ላይ፡ ወንድ እና ሴት፡ በምክንያት እንዲገናኙና የሩካቤ ሥጋ ግዳጅን እንዲፈጽሙ፡ በተፈጥሮ ሥርዓቱን የሠራ፥ ያም ሥርዓት፡ በተግባር ላይ ውሎ፡ መካን የኾነችን ማሕፀን በመክፈትና በማለምለም ጭምር፡ ለፍሬ እንዲበቃ፥ የሚያደርግ፡ እግዚአብሔር ስለመኾኑ፡ ለዚህ ታላቅ ሃይማኖታዊ ቍም ነገር፡ አብነት የሚኾኑንን ማስረጃዎች፡ ለምስክርነት፡ ከቅዱሳት መጻሕፍት መጠቃቀስ ይቻላል። እነዚህም፡ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡-

በሥጋዊው የፍትወት ስሜታቸው፡ ሙታን ለነበሩት፡ በብሉዩ ኪዳን ዘመን፡ ይስሓቅን ለወለዱት፡ ለመቶ ዓመቱ ሽማግሌ፡ ለአብርሃምና ለዘጠና ዓመቷ አረጋዊት ሚስቱ፡ ለሣራ፥ በአዲስ ኪዳኑም ዘመን፡ መጥምቁ ዮሓንስን ለወለዱት፡ ለአረጋዊው ካህን፡ ለዘካርያስና ለአሮጊቷ ሚስቱ፡ ለኤልሣቤጥ፡ አስፈላጊውን የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት እንዲያደርጉና እንዲፈጽሙ፡ እግዚአብሔር፡ የሙሽርነታቸውን ተፈጥሮአዊና ተአምራዊ የፍቅር ስሜትና ኃይል፡ መልሶ እንዳሳደረባቸው ይታመናል።

ይህ ብቻ አይደለም፤ "የእግዚአብሔር ወዳጅ!" የተባለው፥ ከእርሱ፡ ከፈጣሪውም ጋር፡ ባለቃል ኪዳን ተዋዋይ ለመኾን የበቃው፡ ይኸው፡ የመቶ ዓመቱ ሽማግሌ አብርሃም፡ ከሚስቱ ከሣራ፡ ይስሓቅን ከመውለዱ በፊት፡ ሚስቱ ካልኾነችው፡ ከአጋር ጋር፡ የመኝታና የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት አድርጎ፡ የመጀመሪያ ልጁን፡ እስማኤልን በወለደ ጊዜ፡ ይህ ድርጊቱ፡ በእነርሱ፡ በባልና ሚስቱ፥ በኅብረተሰባቸውም ዘንድ፥ በእግዚአብሔርም ዘንድ ሳይቀር፡ እንደኃጢአት ተቆጠረን? "ኃጢአት ነው!" ተብሎስ፡ በቃል ተነገርን? በብራና ላይ ተጽፎስ፡ በኃጢአትነት ተፈረጀን? ይህ ኹሉ፡ ጨርሶ አልኾነም። 'ለምን?" ቢሉ፡ ኃጢአት አይደለማ!

በሓሰት፡ "ኃጢአት ነው!" ብለው፡ በኃጢአትነት የፈረጁት፡ ራሳቸው፡ "ኃጢአት"፡ የኾኑት፡ ዲያብሎስና የእርሱ ጭፍሮች የኾኑ፡ ክፉዎች ሰዎች ናቸው። "ኃጢአት" ማለት፡ የቃል ለቃል ትርጉሙ፡ "ኃጢአ-ጽድቅ"፥ ማለት ነው፤ "እውነትን ያጣ"፥ "እውነት የሌለችበት" ማለት ነው፣ እርሱም፡ "ሓሰት" ተብሏል። ስለዚህ፡ "ሓሰት" የ"ኃጢአት" ሌላው ስሙ መኾኑን፡ ምንጊዜም ማጤን ይገባል።

እውነታው ይህ ካልኾነ፡ ታዲያ! ሽማግሌው አብርሃም፡ የሚስቱ የሣራ ገረድ ከኾነችው፡ ከግብፃዊቷ ከአጋር ጋር፥ ከጋብቻ ውጪ፡ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለማድረግ፡ የፈቃደኛነቱና የፍላጎቱ ስሜት፡ በዚያ የእርጅና ዕድሜው፡ እንዴት ተነሣሣበት? ዐየለበትስ? ይህን ስሜት መፍጠር፥ ኃይሉን መስጠትና ድርጊቱንም እንዲፈጽም ማድረግ የሚቻለውና የተቻለው፡ እርሱ ማነው? እግዚአብሔር ነዋ! ታዲያ! ያ እውነተኛ ኹኔታ፡ በዛሬዎቹ፡ ኪዳናዊና ኪዳናዊት የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ የማይኖርበት፥የማይፈጸምበትስ፡ ምን ምክንያት አለ? የለም።

ሣራም፡ በመቶ ሃያ ሰባት ዓመቷ ከሞተች በኋላ፡ "ሽመገለ፤ በዘመኑም አረጀ፤ ዐፈጀ፤" የተባለው፡ ይኸው፡ አብርሃም፡ ቀድሞ፡ ራሱ፡ ከመልከ ጼዴቅ፥ ኋላም፡ ከመልከ ጼዴቅ የትውልድ ሐረግ ከሠረፀችው፡ ከኢትዮጵያዊቷ ኬጡራ ባገኘው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቱ፡ እርሷን አግብቶ፡ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር በኾነችው፡ "ምድያም" በተባለችው ምድር ስለሚኖሩ፡ "ምድያማውያን" የተባሉ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቹን የወለደው፡ በስንት ዓመቱ መኾኑን ለመገመት፡ ለማንም የሚሳን አይደለም።

ደግሞስ፡ "ከእንግዲህ ወዲህ፤ ስምህ፡ '‹እስራኤል› ይባል እንጅ፡ ‹ያዕቆብ› አይባል! ከእግዚአብሔር፥ ከሰውም ጋር ታግለህ አሸንፈሃልና!' የተባለው ያዕቆብ፡ "ራሔል" እና "ልያ" ከተባሉት፡ ኹለት ሚስቶቹ፥ ከእነርሱ ኹለት ገረዶችም፡ ፲፪ (አሥራ ኹለት) ልጆችን ሲወልድ፡ ይህ ድርጊቱ፡ ኃጢኣት ኾነበትን? በራሱም፥ በቤተሰቡና በወገኖቹ፥ በእግዚአብሔርም ዘንድ፤ እንደመልካም እንጂ፡ እንደጥፋት፥ እንደበረከት እንጂ፡ እንደኃጢኣት አልተቆጠረበትም።

ይህም ኾኖ፡ "እንደአዳምና ሔዋን፡ አንድ ወንድ፡ ለአንዲት ሴት፥ አንዲት ሴት፡ ለአንድ ወንድ"፡ የሚለውን፡ ሥርዓተ እግዚአብሔር አክብረውና አጽንተው በሚኖሩት፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ፡ ይህ፡ የያዕቆብ አድራጎት፡ ቅዱሱን የኢትዮጵያዊነት ኪዳን እንደማፍረስ ስለሚቆጠር፡ እንኳንስ፡ ሊፈጸም፡ ጭርሱኑም አይታሰብም።

በዚህ ረገድ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት፡ ፈጽሞ የበቃው፡ እስራኤላዊ የነበረው ሙሴ፡ ወደኢትዮጵያ መጥቶና በዚያ ኖሮ፡ ኹለት ልጆችን ከወለደችለት፡ ከኢትዮጵያዊቷ ሚስቱ፡ ከሲጳራ ጋር በፈጸመው ጋብቻውና የትዳር ኑሮው ምክንያት፡ ከእስራኤላውያኑ ወገኖቹ የደረሰበት የተቃውሞ ፈተና፡ እዚህ ላይ ሊጠቀስ የሚገባው ነው። ይኸውም፡ ሙሴ፡ በዚሁ ኢትዮጵያዊነቱ፡ ያለውልውል ከመጽናቱ የተነሣ፡ እስራኤላዊቷ እኅቱ፡ ሚርያምና እስራኤላዊው ወንድሙ አሮን ሳይቀሩ፡ በጠላትነት ተነሥተውበት፡ በእግዚአብሔር ቍጣና መቅሠፍት እንደተገሠፁ፡ ተጽፎ፡ እስከዛሬ የሚነበበው ዜና መዋዕል ነው።

በመጨረሻ፡ "የልቤን ፈቃድ የሚፈጽም፡ ታማኙ አገልጋዬ!" ብሎ፡ እግዚአብሔር የመሰከረለትንና ለማካተቻው ፩ኛ ቃል ኪዳኑ ተዋዋይ ያደረገውን፡ ጻድቁን ነቢይ፡ ንጉሥ ዳዊትን በሚመለከት፡ በዚህ ረገድ፡ እዚህ ላይ ሊወሳ የሚገባው ዝክረ ነገር አለ።

ያም፡ ወራሴ መንግሥቱ የኾነውን፡ የልጁን የንጉሥ ሰሎሞንን እንተወውና፡ ራሱ፡ አባትዮው፡ ንጉሥ ዳዊት፡ ከብዙ ሚስቶቹና ቁባቶቹ፡ ብዙ ልጆችን መውለዱ ሳያንስ፥ ያም፡ እንደኃጢኣት ሳይቈጠርበት፥ ሌላው፡ በድፍረት የፈጸመውን፡ ታላቁን ግፍ የሚያወሳው ነው።

ታላቁ ግፍ የተባለውም፡ በጦር ግዳጅ ላይ ተሠማርቶ፡ እየተጋደለ ያለውን፡ የታማኝ አገልጋዩን፡ የኢትዮጵያዊዉን፡ የኦርዮንን፡ አንዲት የቃል ኪዳን ሚስት፡ ቤትሳባን፡ በሥውር መድፈሩ ብቻ ሳይኾን፡ እርሱን ባሏን፡ በግፍ ተንኰል ካስገደለ በኋላ፡ እርሷን፡ በገሃድ፡ ሚስት በማድረግ፡ የፈጸመው ወደር የሌለው በደል ነው። ያን የመሰለው ከባድ ጥፋት፡ በንስሓ ምሕረት ተወግዶና እንዳልተፈጸመ ተቆጥሮ፡ መለኮታዊው ፈቃድና ዕቅድ፡ እስከመጨረሻው እንደቀጠለ ይታወቃል።

የአብርሃም የወንድም ልጅ የኾነው ሎጥም፡ ከኹለት ሴቶች ልጆቹ መውለዱ፡ እንዲሁ፡ እንደኃጢኣት ሳይቆጠር፡ ከእነርሱ፡ የዘር ሓረግ የተወለደችው፡ ሩት፡ የዳዊትን ቅድመ ቅድም አያት የኾነውን፡ ቦኤዝን አግብታ፡ ለቃል ኪዳኑ፡ ዘለዓለማዊ ንጉሠ ነገሥት፡ ለኢትዮጵያዊው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ቅድመ ቅድም አያት በቅታለች። (ዘፍጥ. ፩፥ ፪፮-፳፰፤ ፪፥፲፰-፳፭። ፲፮፥ ፩-፲፮፤ ፲፯፥ ፲፭-፲፰፤ ፳፫፥ ፩-፪፤ ፲፱፥ ፴-፴፰፤ ፳፬፥ ፩፤ ፳፭፥ ፩-፰፤ ፳፱፥ ፲፫-፴፭፤ ፴፥ ፩-፳፬፤ ፴፪፥ ፳፪-፴፪። ዘኍ. ፲፪፥ ፩-፲፭። ሩት ፪፥ ፩-፪፤ ፬፥ ፲፫-፳፪። ፪ኛ ሳሙ. ፲፩፥ ፩-፳፯፤ ፲፪፥ ፩-፴፩። ማቴ. ፩፥ ፩-፲፮።)

እነዚህ ኹሉ ዝክረ ነገሮች፡ አረጋግጠው የሚመሰክሩት፡ በሰብኣውያን ፍጡራን ዘንድ፥ ይልቁንም፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" በተባሉት ዘንድ፡ በጋብቻም ኾነ ከጋብቻ ውጪ፡ ለሰው ልደት፡ መነሻ ምክንያት የኾነው፥ በወንድና በሴት መካከል የሚደረገው፡ በመጀመሪያ፡ መተያየቱ፥ ትውውቁና መነጋገሩ፥ ከዚያም፡ ለመቀራረብ ያለው የፍላጎት ግፊት፡ በሰውነት ውስጥ መነሣሣቱ፥ ቀጥሎ፡ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነትን ለማድረግ እስከመሻት በሚያደርስ የፍቅር ስሜት መፈቃቀዱና ለጋብቻ መብቃቱ፥ በመጨረሻም፡ ሩካቤ ሥጋን መፈጸሙና በፅንስ ፍሬ መደምደሙ፡ ይህን ኹሉ የድርጊት ሥርዓታዊ ኺደት፡ የፍጥረቱ ሠሪና ባለቤት የኾነው እግዚአብሔር ሳያውቀውና ሳይፈቅደው ሊወጠን፥ ሊካኼድና ሊከናወን እንደማይችል ነው።

ያም፡ የድርጊት ሥርዓታዊ ኺደት፡ በኹለንተናዊ መልኩና ይዘቱ፡ መልካም እንጂ፡ ክፉ፥ ጽድቅ እንጂ፡ ኃጢኣት እንዳልኾነ ነው። ምናልባት ግን፡ "የለም! ኃጢኣት ነው!" ብሎ በራሱ የሚያስብ ሰው ቢኖር እንኳ፡ ያም እኮ፡ ቀድሞም፡ በብሉይ ኪዳኑ፥ በይበልጥም፡ በእግዚአብሔር አብና በድንግል ማርያም ልጅ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት በተገኘው የንስሓ ስርየት፡ ለአንዴና ለዘለዓለሙ ተወግዷል።

እዚህም ላይ፡ "ብፁዓን፡ እለ ተኀድገ ሎሙ ኃጢኣቶሙ፤ ወእለ፡ ኢሓሰበ ሎሙ፡ ኵሎ ጌጋዮሙ። ብፁዕ ብእሲ፡ ዘኢኈለቈ ሎቱ፡ እግዚአብሔር ኃጢኣቶ፤ ወዘአልቦ ጽልሑት፡ ውስተ ልቡ።" ማለትም፡ "ኃጢኣታቸው፡ ይቅር የተባለላቸው፥ በደላቸውም ኹሉ የተተወላቸው፡ ቡሩኮች ናቸው። በልቡ፡ ተንኰል የሌለበት፥ ከዚህም የተነሣ፡ እግዚአብሔር፡ ኃጢኣቱን የማይቈጥርበት ሰው፡ ቡሩክ ነው።" የሚለው፡ የእግዚአብሔር ቃል የተነገረው፡ እንደእነዚህ ላሉት መኾኑን፡ ማስተዋል ይገባል። (መዝ. ፴፩፥ ፩-፪።)

በክፉዎች ዘንድ፡ "ኃጢአት ነው!" ተብሎ የተፈረጀውን፡ ማናቸውንም ድርጊት፥ እዚህ ላይ የምንነጋገርበትን፡ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነትን ጭምር፡ ስማቸውና ዝክረ ነገራቸው፡ ከዚህ በላይ የተወሳው ቅዱሳንና ቅዱሳት፥ እነርሱን የመሰሉትም ሰዎች ኹሉ፡ ሲፈጽሙት እኮ፡ እግዚአብሔር የሠራው፡ የተፈጥሮ ሥርዓት ስለኾነ፡ "መልካም፡ የጽድቅ ምግባር ነው!" ብለው እንጂ፡ "ኃጢአት ነው!" ብለው አይደለም።

ይህ እውነታ፡ አበክሮና አጠንክሮ የሚያስገነዝበን፡ አንድ ቍም ነገር አለ፤ ይኸውም፡ ማንኛውም፡ ሰብአዊ ፍጡር፡ በተቃወሰ አስተሳሰቡ፡ "ጽድቁን፡ 'የለም! ይህ፡ ኃጢአት ነው!' ካለ፡ በእርሱ ዘንድ፡ ያ ጽድቅ፡ ኃጢአት ይኾናል!" የሚለውን፡ ዘይቤ ነው። ቀድሞም ኾነ ዛሬ፡ ብዙዎች፡ የዚሁ ዘይቤ ሰለባዎች ኾነው ተቀብለውት፡ ሲሠቃዩበት፡ ይኸው፡ በገሃድና በስፋት ይታያል።

እንግዴህ፡ የነገሮችና የኹኔታዎች አካኼድ፡ መንገዱ፡ ይህ ከኾነ፡ በዚህ ጉዳይ ወሳኙ፡ ቅንም ኾነ ጠማማ፡ የሰው አስተሳሰብ እንጂ፡ እውነታው አይደለም ማለት ነው።

ስለዚህ፡ ልክ፡ በዚሁ መልክ ሊባል የሚችለው፡ "ክፉዎች፡ 'ኃጢአት ነው!' ያሉትን ጽድቅ፡ ደጎች ደግሞ፡ 'የለም! ኃጢአት አይደለም!' ብለው፡ በጤናማውና በትክክለኛው አስተሳሰባቸው፡ በዚያው በጽድቅነቱ ባሕርይ አጽንተው፡ ሊኖሩበትና ሊፈጽሙት ይቻላቸዋል፤ ይገባቸዋልም!" ማለት ነው። አዎን! ስማቸውና ዝክረ ነገራቸው፡ ከዚህ በላይ የተወሳው ቅዱሳንና ቅዱሳት ያደረጉትም፡ ይኼንኑ ነው።

በዚህ መሠረት፡ እግዚአብሔርን መስሎና አኽሎ የሚወለደውን፥ "ሰው" የሚባለውን ሕያው ፍጡር የሚያስገኘው፥ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል፡ በጋብቻ ኾነ ከጋብቻ ውጪ የሚደረገው፡ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት፡ ያለእግዚአብሔር ፈቃድና ትእዛዝ፥ ያለመለኮታዊው ምክንያትና ዓላማም አይኾንም። ያለእግዚአብሔር ፈቃድና ትእዛዝ፥ ያለመለኮታዊው ምክንያትና ዓላማም፡ ያ ሰው፡ መጀመሪያ፡ ዘር ኾኖ፡ በወንዱ አብራክ ውስጥ አይፈጠርም፤ ቀጥሎ፡ የወንዱና የሴቲቱ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት፡ ደርሶ ሊፈጸም፥ የወንዱ ዘር፡ በወር አበባዋ ጠርቶና ለስልሶ፡ ዘሩን ለመቀበል በተዘጋጀው በሴቲቱ ማሕፀን አይፀነስም።

ስለዚህ፡ መፈጠሩና መፀነሱ፡ እንዲህ በሚገለጥበትና በሚታወቅበት፡ በዚህ ሽል ላይ፡ ምንም ዓይነት ጉዳት እንዳይደርስ፡ ኹለቱም፡ ወንዱም፥ ሴቲቱም፡ ብርቱ ጥንቃቄን ማድረግ ይኖርባቸዋል። ያ ዘር፥ ያ ፅንስ፥ ያ ሽል፡ የእግዚአብሔርና የድንግል ማርያም ልጅ፥ ነጋሢና ካህን ነውና! እነዚህ የጸጋ ማዕርጋቱም፡ በቅድሚያ፡ በወንዱ አብራክ ውስጥ ባለው ዘር፥ ከዚያ፡ በሴቲቱ ማሕፀን ውስጥ በተፈጠረው ፅንስ ላይ፡ በመንፈስ ቅዱስን ቅብዓት፡ ለአንዴና ለዘለዓለም ታትመዋልና።

ከዚህ የተነሣ፡ በባለአደራዎቹ ወንድና ሴት ላይ፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ የሚያስከትለው የኃላፊነት ተጠያቂነት፡ በዚያው መጠን፡ እጅግ ከባድ ነውና፡ የሰውኛና ሰይጣናዊ በኾነው፡ በ"ወሊድ መቆጣጠር" ሰበብ፡ በዚህ ሽል ላይ፡ ከፅንሱ ጀምሮ፡ ጉዳት እንዳይደርስ፡ አዎን! ባለዘሩ ወንድና ባለፅንሷ ሴት፡ ለዚያ ፅንስ፥ ለዚያ ሽል፡ ልዩ ጥንቃቄንና ሙሉ እንክብካቤን ሊያደርጉ ይገባቸዋል።

እንግዴህ፡ ብዙ ጠንቆችን እያስከተለ ያለውን፡ ሰዎች የሠሩትን፡ "የወሊድ መቆጣጠር"ን አማሳኝ ዘዴ ትተን፡ ዘለዓለማዊ ጸጋና በረከት የመላበትን የቍጥጥሩን መለኮታዊ ሥልጣን፡ የሰብአዊው ልደት፡ ፈጣሪና ከዋኝ ለኾነው፡ ለቸሩ አምላካችን፡ ለልዑል እግዚአብሔር እንተውለት!

## ቅዱሱ ኪዳን
## ያቀረበው፡ ሉዓላዊ ጥሪ፡

"የወሊድ መቆጣጠርን" ጠንቅ ካመጡት ምክንያቶች አንዱ፡ ፀረ-እግዚአብሔር የኾኑ፡ እምነተ ቢስ ሰዎች፡ በእየራሳቸው፡ ሓሳዊ አእምሮ ውስጥ የፈጠሩት፡ የሌለና ምትሓት የኾነ ሰይጣናዊ አስተሳሰብ፡ የደካሞችን ቀልብ ስቦ፡ ለዚያ ጎጂ አስተሳሰብ ተገዥ ማድረጉ ነው።

"የወሊድ መቆጣጠርን" በሚመለከት፡ ግልጽ የኾነው እውነታ፡ እንዲህ፡ በሚል ቃል፡ ተጠቃልሎ ቀርቧል፡-

"የወሊድ መቆጣጠር"፡ በጋብቻም ኾነ ከጋብቻ ውጪ፡ በልጆች መወለድና በብዛታቸው መጠን ረገድ፡ በግለሰብ፥ በቤተሰብና በኅብረተሰብ ላይ የሚደርሰውን፡ ባዕዳኑና ዘመኑ ያመጡትን፡ ከባድና የተለያየ ብዙ ችግር፡ እንዴት ልንቋቋመው እንችላለን? ስለማንችል፡ መፍትሔው፡ ‹የወሊድ መቆጣጠር› ነው!' ብለው የወሰኑ ወገኖች፡ በዚሁ ዘዴ አምነውበት፡ የሚፈጽሙት ኾኖ፡ በይፋ ይሠራበታል።

ይህም የኾነው፡ እነዚሁ ወገኖች፡ ልጆች፡ ያለእግዚአብሔር ፈቃድና ፈጣሪነት እንደማይወለዱ፥ ሲወለዱም፡ የእግዚአብሔርና የቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ልጆች፥ የመንግሥታቸው ወራሾችና አገልጋዮች ካህናት ኾነው እንደሚወለዱ፥ ከዚህ የተነሣም፡ በሕፃናቱም ኾነ፥ በሰውነት ወላጆቻቸው ዘንድ፡ በመለኮታዊው በረከትና ጸጋ፡ የተትረፈረፋቸው ኾነው ከሚኖሩ በቀር፡ በነፍሳዊው እውቀትና ጥበብ፥ በሥጋዊው ገንዘብና ንብረት፥ በመንፈሳዊው ሥልጣንና ኃይልም በኩል፡ ምንም የሚያጡት ነገር ሳይኖር፡ ፍላጎታቸው ኹሉ ተሟልቶ፡ ህልውናቸውን በመልካም እንደሚቀጥሉ የሚያረጋግጠውን፡ እግዚአብሔር፡ ለሰው ልጆች የሰጠውን፡ ይህን፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታቸውን በመካድ ነው።

እንግዴህ፡ እውነታው ይህ ከኾነ፡ በምድርና በሰማያት ሰፍና፡ ፍጥረተ ዓለሙን የምትመራውና የምትጠብቀው፥ የምታስተዳድረውና የምትመግበው፡ ይህች፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ራሷን፡ ለዓለሙ ኹሉ የሰው ልጆች፡ በአዋጅ የገለጠችው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** ዓለም፡ ከተፈጠረ ጀምሮ ስታደርግ እንደኖረችውና ዛሬም እያደረገች እንዳለችው፥ ወደፊትም፡ በዚሁ መልኩና ይዘቱ እንደምትቀጥለው ኹሉ፡ በዚህ፡ በ"ወሊድ መቆጣጠር" እና ከእርሱ ጋር በተያይዘ ጠንቆች ተማርካችሁ ለምትሠቃዩ ግለሰቦች፣ ባለትዳሮችና ቤተሰቦች! የምትላችሁን ስሙ!

"ሥጋዊዉን፥ ነፍሳዊዉንና መንፈሳዊዉን ጤናችሁንና ሕይወታችሁን፥ ሰላማችሁንና ደስታችሁን የሚያቃውሰውን፡ ይህን፡ "የወሊድ መቆጣጠር" የምታደርጉት፡ ስለምትወልዷቸው ልጆች መብዛትና ማነስ፡ ቍጥጥር ለማድረግ ብቻ ሳይኾን፡ ሌሎች፡ እጅግ ብዙ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ፤ እነርሱንም፡ እዚህ ላይ መዘርዘሩ፡ የሚያስፈልግ አይኾንም። ምክንያቶቹና ሰበቦቹ፡ የቱንም ያህል የበረከቱ ይኹኑ፡ ለኹሉም፡ እኛ፡ የሰማዩ አባታችሁና የሰማይዋ እናታችሁ፡ መፍትሔውን እናደርጋለን።

"በዚህ፡ የአባትነት እና የእናትነት ጥሪያችን መሠረት፡ በጋብቻም ኾነ ከጋብቻ ውጪ የተፀነሱና የተወለዱ፥ ወደፊትም፡ የሚፀነሱና የሚወለዱ ቢኖሩ፥ የምታደርጉትም ሩካቤ ሥጋ፡ በፈቃዳችሁም ኾነ ያለፈቃዳችሁ የተፈጸመና የሚፈጸም ቢኾን፡ ያለእግዚአብሔር ፈቃድ የሚኾን፡ ምንም ነገር የለምና፥ ሕፃናቱም፡ ያለእርሱ ፈጣሪነት አይፈጠሩምና፥ ከተፈጠሩም፡ እርሱ የሚፈጥራቸው፡ ለበጎ የሕይወት ዓላማ ነውና፥ ለእነርሱም፡ የሚያስፈገው ኹሉ፡ በምድር ላይ ተዘጋጅቶ አለና፡ እባካችሁ! አታስወርዷቸው! ፅንሱንም አትከልክሉ!

"የፈጠርኋቸው እኔ እግዚአብሔር፡ አባታቸው ነኝና፥ እኔም፡ ድንግል ማርያም፡ የዘለዓለም እናታቸው ነኝና፥ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ፡ የሚያስፈልጋቸውንም ኹሉ፡ እነሆ፥ አኹንም፥ ምንጊዜም፡ በምድር ላይ አዘጋጅተን እንጠብቃለንና፡ ለእኛ ስጡን! እነርሱን ብቻ አይደለም፤ በእነርሱ ምክንያት፡ እናንተም፡ በችግር ላይ ከኾናችሁ፡ እናንተም፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችን፥ ነጋሢዎቻችንና ካህናቶቻችን ናችሁና፡ ቤታችን የኾነው ፍጥረተ ዓለሙ፡ ቤታችሁ፥ ሀብታችን፡ ሀብታችሁ፥ መንግሥታችን፡ መንግሥታችሁ ናቸውና፡ ወደእኛ ኑና ዐብራችሁን ኑሩ!

"ይህ ጥሪያችን፡ አሳዳጊ ላጡና ለሙት ልጆች፥ በሥጋ የወለዷቸውን ለማያውቁና ችግረኞች ለኾኑ ልጆች፥ ደግሞም፡ የእነርሱ ባለአደራዎች ለኾናችሁና ለተቸገራችሁ ትልልቆች ኹሉ ነውና፡ ለእናንተም ጭምር፡ እኔ እግዚአብሔር አባታችሁ፥ እኔም፡ ኢትዮጵያ፡ እናታችሁ ነንና፡ እናንተም፡ እንደሌሎቹ፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችን፥ ነጋሢዎቻችንና ካህናቶቻችን ናችሁና፡ ቤታችን የኾነው ፍጥረተ ዓለሙ፡ ቤታችሁ፥ ሀብታችን፡ ሀብታችሁ፥ መንግሥታችን፡ መንግሥታችሁ ናቸውና፡ እናንተም፡ እንደእነርሱ፡ ወደእኛ ኑና ዕብራችሁን ኑሩ!

"ይህ የጥሪ መልእክታችን የተላለፈላችሁና ቃላችንም በተግባር ላይ የሚውለው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ነው። አኹን የምትኖሩባትን ምድር ጨምሮ፡ በፍጥረተ ዓለሙ መልታና ሰፍና ያለችውን፡ እርሷንም፡ ከጥንት መሥርተን የምንመራትና የምናስተዳድራት፥ የምንጠብቃትና የምንመግባት፡ እኛ ነን። ከዚህ የልዕልና ምስፍናዋና የህልውና ምልዓቷ የተነሣ፡ እዚያው፡ እናንተው ዘንድ፡ በውስጣችሁና በአካባቢያችሁ፡ በእውንነቷና በሕያውነቷ ተገልጣ ትገኛለች። እኛም፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ አጠገባችሁ ኾነን፡ እያነጋገርናችሁ ነን።

"በእናንተ በኩል፡ በቅርቡ የላክንላችሁን፡ የዐዋጅ ቃላችንን ተከትላችሁ፡ እየራሳችሁን፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችሁና በእውነተኛው መንፈስ ቅዱሳዊ አምልኳችሁ አስተካክላችሁና አጽንታችሁ፡ ለእግዚአብሔራዊው ምንነታችሁና ማንነታችሁ አብቅታችሁ ስትገኙ፡ እኛንም፡ በቀጥታ፥ በእውን ታገኙናላችሁ። በዚያን ጊዜና ከዚያ በኋላ፡ የምትፈልጉትና የሚያስፈልጋችሁ ኹሉ ቀርቦላችሁ ታገኙታላችሁ።

"የዚችው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን አገልጋዮች ካህናት፥ ለእናንተም፡ ኪዳናውያን ወንድሞቻችሁና ኪዳናውያት እኅቶቻችሁ የኾኑ ልጆቻችንና ነጋሚዎቻችን፡ በየአቅራቢያችሁ አሉና፥ በዚህ የጎዋ መድረክ፥ በሌላውም መገናኛ መስመር፡ መነጋገር፥ መጻጻፍና መላላክ ትችላላችሁ። በእነርሱም አማካይነት፡ የእኛ የኾነው መልእክት፡ ለእናንተ፥ የእናንተ የኾነውም፡ ለእኛ ሊተላለፍና ሊደርስ ይችላል።

"ይኼን፡ የዘለዓለም አባታችሁን፡ የእግዚአብሔርን እና የዘለዓለም እናት አገራችሁ ኢትዮጵያን፡ የፍቅር ጥሪ ሰምታችሁና ተቀብላችሁ ለመፈጸም ወደኋላ አትበሉ! አታመንቱ! አታወላውሉ! አትጠራጠሩ!

"እናንተ፡ በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖታቸውና ምግባራቸው፡ እውነተኞችና ጠንካሮች የነበሩት፥ በነቢያትም ቃል፡ "ብፁዕ ሕዝብ፡ ዘእግዚአብሔር አምላኩ! ሕዝብ ዘኀረየ ሎቱ ለርስቱ!" ማለትም፡ "እግዚአብሔርን፡ አምላኩ ያደረገ፥ እግዚአብሔርም፡ ርስቱ ያደረገው ሕዝብ፡ ምስጉን ነው!" የተባሉ፡ የእነዚያ፡ የቀደሙት ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ወገኖቻችሁ ትውልድ ስለኾናችሁ፡ የእነርሱን፡ የታማኝነትና የጽናት ባሕርይ፡ እናንተም መልሳችሁ ያዙ! ለዘለቄታው የሚበጃችሁ፡ እርሱ ነውና! (መዝ. ፴፪፥ ፲፪።)

"በእውነተኛ ንስሓችሁ፥ ፈቃዳችሁና ምርጫችሁ፡ እየራሳችሁን፡ ለዚህ የሕይወት ጸጋ አብቅታችሁ እስክናገኛችሁ ድረስ፡ አይዟችሁ፡ የእኛ የቃል ኪዳን ጥበቃ፥ ሰላምና ፍቅር፡ ምንጊዜም አይለያችሁም።"

በመንፈስ ቅዱስና በቅድስት እናታችን ድንግል ማርያም የተባረከውን ሱባኤያችንን፡ በያለንበት ፈጽመን፡ የበዓለ ትንሣኤዋን ዝክር ለምናከብርባት ዕለት፡ ጠብቆ የሚያደርሰንን ቸሩ ፈጣሪያችንን፡ ከነእናቱ እናመሰግነዋለን!

ነሓሴ ፱ ቀን፥ ፳፻፮ ዓመተ ምሕረት።

በቅዱሱ ኪዳን፡ አገልጋይ ወንድምህ፡-
ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ።